# ኀንጉል ኮላሴ

Gli Italiani in Africa Orientale በሚባለው መጽሐፉ ውስጥ አንጀሎ ዴል ቦካ ስለፊታውራሪ ኀንጉል ኮላሴ ጽፏል። አንጀሎ ዴል ቦካ ሲተርክ "…..ደጃዝማች አፈወርቅ ቆስለው ከሞቱ በኋላ ጄኔራል ግራዚያኒ ቆራሄን በቀላሉ ለመያዝ በመቻሉ ተደሰተ። የማካናይዝ ጦር አዛዥ የሆነውን ኰሎኔል ማሌቲንን (Malettin) ጠርቶ 'ታንኮችንና ብረት ለበስ መኪናዎችን አስቀድመህ ወታደሮችህን በመኪና ጭነህ እየገሰገስህ ከቆራሄ ባመለጠው በኢትዮጵያ ጦር ላይ ደርሰህ ሁሉንም እንድትማርክ' ብሎ አዘዘው።

"ምንም እንኳ ጊዜው ዝናብ ሆኖ ቢያስቸግርም የታዘዘው የኢጣሊያ ጦር ቀብሪደሃርንና ኡራን ዶብን ለመያዝ ቻለ። የኢጣሊያ ጦር ወደፊት በሚገሰግስበት ጊዜ ባንዳንድ ወደኋላ በቀሩ ኢትዮጵያውያኖች ላይ አደጋ እየጣለ ቢጓዝም ጉዞው በጭቃው ምክንያት በጣም አስቸጋሪ ነበር። ከጭቃው ብዛት የተነሣ መኪናዎቹ በየቦታው በየጭቃው ውስጥ እየገቡ በመያዛቸው እጅግ አድካሚ ጉዞ ነበር።

"የኢጣሊያ ጦር በዚህ ሁኔታ በሚጓዝበት ጊዜ በኢትዮጵያ በኩል ለቆራሄው ጦር እርዳታ እንዲሰጥ በጥሩ ሁኔታ የታጠቀ አዲስ ጦር በጨርጨር (ሐረርጌ ውስጥ) ገዥ በፊታውራሪ ኀንጉል ኮላሴ አዛዥነት ተልኮ ነበር። ይህ የኢትዮጵያ ጦር ጀረር የሚባለው ወንዝ፣ ፋፈም ከሚባለው ወንዝ ጋር ከሚገናኝበት ሐነለይ ከሚባለው ቦታ ሕዳር 11 ቀን (እ.ኤ.አ.) ንጋቱ አካባቢ ላይ ሲደርስ የኢጣሊያን ጦር በድንገት አዩት።

"የኢትዮጵያውያኖቹ ጦር 500 ያህል ሰዎች ያሉበት ነው። ኢትዮጵያውያኖቹ የኢጣሊያን ጦር እንዳዩ ጀረር ወንዝ ገብተው ባገኙት ጉድጓድና በየዋርካዎቹ ሥር እየተኙ አደፈጡ። የኢጣሊያ ጦርም በየመኪናዎቹ እንደሆነ ሲጓዝ ከኢትዮጵያውያኖቹ ፊት ለፊት ሲደርስ ኢትዮጵያውያኖቹ በእርምታ ተኩስ ተኮሱ።

"በመኪና ይጓዙ ከነበሩት መኰንኖች አንዱ ቴኒንቲ (መቶ አለቃ) ጋብርኤሌ ቬሪ (Gabriele Verri) ስለዚያች ጊዜ ሁኔታ ሲጽፍ '…ይህ ጦርነት ሳናስበው የደረሰ ድንገተኛ አደጋ ስለነበረ የጦር አዛዣችን ታንኮቹን፣ ፈጣን መትረየስ ተኳሾቹንና የሱማሌ ወታደሮችን እያጣደፈ ቢያስተኩስም የተኩሱ ውጤት ኢላማውን የማይመታ ነበር። በጦራችንም መካከል አስተባባሪና መገናኛ ያልተዘጋጀ ስለነበር ሁሉም ተደናግጦ ድብልቅልቅ ያለ ሽብር ሆነ።…..ታንከኛው ካፒቴን ላፖ ሞሊኞኒ (Lapo Molignoni) የታንኩን መስኮት ሳይዘጋ በድፍረት ወደ ውጊያው ሲገባ በኢትዮጵያውያኖች ተኩስ ተመለሰ።….' ብሏል።

"በዚህ ሁኔታ ሶስት ሰዓት ሙሉ ከባድ ውጊያ ተካሄደ። 9 (በኛ 3) ሰዓት ሲሆን አንዲት ፊያት ታንክ የጀረርን ወንዝ ለመሻገር ወደ ወንዙ ሲገሰግስ የታንኩ እግር በአሸዋ ተውጦ ቆመ። ይህ ታንክ ለኢትዮጵያውያኖቹ ተመቻችቶ ስለቆመ መትረየስ ተኳሾቹ የኢትዮጵያ ወታደሮች የጥይት ዝናብ ያወርዱበት ጀመር።

"ኰሎኔል ማሌቲን፣ ካፒቴን ሞሊኞኒን ጠርቶ እንደምንም አድርጋችሁ ያን ታንክ አውጡ ብሎ አስቸኳይ እና ጥብቅ ትእዛዝ አዘዘ። ወዲያውኑ ያን በአሸዋ የተያዘ ታንክ ለማውጣት ሁለት ታንኮች ተላኩ። እነዚህም የተላኩት ሁለት ታንኮች ገና ከወንዙ ውስጥ ሲገቡ እነሱም በአሸዋው ተይዘው ቆሙ። ሌላ አራተኛ

ታንክ ተላከ ። ይህን አራተኛውን ታንክ እንዳይነቃነቅ የጓንጉል ወታደሮች በተኩስ አፍነው አቆሙት ።

"እነኚያ በየዋሻውና በየዛፉ ሥር የመሸጉት የጓንጉል መትረየስ ተኳሾች ቀል ጣፋና ጥሩ አነጣጣሪዎች ስለነበሩ ወደቆሙት ታንኮች ሰው እንዳይደርስ አድርገው በጠላታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱበት ።

"ኰሎኔል ማሌቲን ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ ሲናገር '....በየዋሻውና በመትረየስ ተኳሾች ሁሉ ላይ ቤንዚን (?) ተረጭቷል ። ብዙ የጅ ቦምቦች ጥለንባቸዋል ። በመትረየስና በመድፍም ክፉኛ ተታኩሰናል ። ግን ምንም ውጤት አላገኘንም ። .........'ብሏል ። ቴኔንቴ ቬሪ እንደጻፈው ደግሞ '.....በኰሎኔል ማሌቲን የሚመራውን ጦር እንደዚያ አስቸግሮ ወጥሮት የዋለው ፣ በኢጣሊያኖችም ሠፈር ሽብር የዘራውና ምስቅልቅላችንን ያወጣው የፊታውራሪ ጓንጉል ትንሽ ጦር ነው ። ፊታውራሪ ጓንጉል ወታደሮቹን በሙሉ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ አድርጐ እሱ ራሱ አርባ ወታደሮች ብቻ ይዞ ጀረን ወንዝ ውስጥ መሸገ ። በእነዚህ አርባ ሰዎች ብቻ የኢጣሊያን ጦር ገትሮ በማቆም አሸበረው ።.........' ብሏል ። ......." በማለት አንጀሎ ዴል ቦካ ጽፏል ።

በዚያ ዕለት የተደረገውን ውጊያ የገላገለው የጀምበር መጥለቅ ነው ። ከቀኑ 12 ሰዓት ሲሆን አዳዲስ ጦር እየተካ ይዋጋ የነበረው የኢጣሊያ ጦር ድል ሆኖ አፈገፈገ ። ጀረር ወንዝ ውስጥ መሽገው ከነበሩት ከጓንጉል አርባ ወታደሮች መሀል እየቆሰሉም ፣ እየሞቱም ቢቀነሱም ያለ ተተኪ ተራፊው ወታደር ሲዋጋ ዋለ ። ማታገደማ የኢጣሊያ ጦር ወደኋላ ከሸሸ በኋላ ኢትዮጵያውያኖቹ ከብዙ የሱማሌ ወታደሮች ሬሣዎች መሀል ሰባት የኢጣሊያኖችን ሬሣ አገኙ ። መትረየሶችና ብዙ ጥይት ማርከው አነሱ ። እነኚያ በአሸዋ ተይዘው የነበሩ ሶስት ታንኮችና ለርዳታ የተላከው አራተኛው ታንክም በኢትዮጵያውያኖች እጅ ገቡ ። ፍራንቼስኮ አስኮሊ እንደፃፈው በዚያ ቦታ ኢትዮጵያውያኖቹ 66 የጠላት ሬሣ አስቆጠሩ ይላል ።

፣ከአርባዎቹ የፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ ምርጥ ወታደሮች መሐል አንደኛው ታናሽ ወንድማቸው ኃይለማርያም ኮላሴ ነበሩ ። ኃይለማርያም ኮላሴ በቀኑ ውሎ የሠሩትን ጀብዱ ግዳይ ለመጣልና ከወንድማቸው ፊት ለመፎከር የገደሉትን የኢጣሊያ ሬሣ ከታንኩ ውስጥ ሰጠኝ ከሚባል ወታደር ጋር አወጡ ። ኃይለ ማርያም ኮላሴ ከወንድማቸው ከፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ ፊት ግዳይ ጥለው ፎክረው እንዳበቁ ታማኝ አሽከራቸው ሰጠኝ ከታንኩ ውስጥ ሰዓት አገኘሁ ብሎ ለኃይለማርያም ኮላሴ የጅ ቦምብ አሳያቸው ። በዚያን ጊዜ ከጥቂት የኢትዮጵያ ወታደሮች በስተቀር የጅ ቦምብን የሚያውቅ አልነበረምና ኃይለማርያም ኮላሴ ወታደር ሰጠኝ ሰዓት አገኘሁ ብሎ ያሳያቸውን ነገር እንዳዩ "የእነኚህ ተንኮለኞች ነገር አይታወቅምና ወዲያ ጣል " ብለው ሰጠኝን አዘዙት ። ሰጠኝ በአዛዡ ትእዛዝ መሠረት የያዘውን የጅ ቦምብ ባለማወቅ ከዚያው ከመሀላቸው ጣለው ።

ያ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያልታወቀው የጅ ቦምብ ፈንዳ ። ወዲያውኑ ስምንት ሰዎች ሞቱ ። ከነዚህም ከሞቱት ስምንት ሰዎች መሀል አንደኛው ወታደር ሰጠኝ ነው ። የጦሩ አዛዥ የነበሩት ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ ከሁለት ቦታ ቆሰሉ ። ጀግናው ኃይለማርያም ኮላሴም ክፉኛ ቆሰሉ ። ቀኑን ሙሉ ቦታውን አለቅ ብሎ የዋለው የኢትዮጵያ ጦር ፣ ባንዲት የጅ ቦምብ ምክንያት በአዛዦቹ መቁሰል ተሸብሮ ተፈታ ። ሁለቱ ወንድማማቾችም በቃሬዛ ወደ ደገሀቡር ተወሰዱ ። በደገሀቡርም ስዊድን ሆስፒታል ገብተው በሕክምና ላይ እንዳሉ ሕዳር 5 ቀን 1928 ዓ.ም ኃይለማርያም ኮላሴ ሞቱ ።

ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ ቁስላቸው ከባድ ስለነበር ወደ አዲስ አበባ ተወስደው ሆስፒታል ገቡ ። ፊታውራሪ ጓንጉል ሆስፒታል እንደተኙ ፒር ኢካች

(Pierre Ichac) የተባለ ጋዜጠኛ አነጋግሯቸው ነበር ። ጋዜጠኛው ላ ጉየራ ኢታሎ ኢትዮፒኔ በተባለው መጽሐፉ እንደጻፈው "……ፊታውራሪ ኀንጉልን አዲስ አበባ ባለው በስዊድን ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ ሲታከም አግኝቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች በታንክ ውስጥ ያሉትን ኢጣሊያኖች እንዴት አድርገው መግደል እንደቻሉ ጠይቄው ነበር ።

"እንዲህ አለኝ ። ኢጣሊያኖች ከፊትና ከኋላ ፣ ከጐንና ከጐንም በተደፈነ የብረት ሣጥን ውስጥ ሆነው ይተኩሱብናል ። እኛ ከፊት ለፊታቸው ተደብቀን ስን መለከት በታንኩ ፊት በኩል ቀናንሽ ቀዳዳዎች እንዳሉ አየን ። በዚያች ቀዳዳ በኩል እያነጣጠርን መተኩስ ጀመርን ። ልክ መተኮስ እንደጀመርን ታንኩ ላይ ተደግኖ የነበረው መትረየስ አፈሙዙ ዝሎ ወደታች አዘነበለ ። በዚህ ጊዜ በታንኩ ውስጥ ያሉት ሰዎች መሞታቸውን አወቅን ። ከዚህ በኋላ በሌላዎቹ በሶስቱ ታንኮች ላይ በዚያችው ዓይነት ቀዳዳ እያነጣጠርን በመተኮስ ሁሉንም ገደልናቸው ብለው አጫወቱኝ ። ……" ሲል ጽፏል ።

ኀንጉል አልተወራላቸውም እንጂ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ጀግኖች ልጆቿ አንዱ ነበሩ ። ኢጣሊያ አዲስ አበባን እንደያዘ ኀንጉል ከሆስፒታል ወጥተው በቃሬዛ ፣ በፊት ወደሚኖሩበት ሜኤሶ ወደተባለው የባቡር ጣቢያ መንደር ሄዱ ። በዚያም ቁስላቸው አልዳነም ነበርና ተኝተው ይታመሙ ጀመር ። ኀንጉል ፣ ሰጦኝ ሳያውቅ ባፈነዳት ቦምብ በደረሰባቸው አደጋ የአልጋ ቁራኛ ይሁኑ እንጂ ስለ ኢትዮጵያ መወረር ማሰባቸውን አልተዉም ነበር ። ይህንንም ከደብዳቤያቸው እንረዳለን ።

ለወንድሞቼ ለባላምባራስ ብርሃኑ መስቀል ወልደ ሥላሴ
ለቀኛዝማች መኩሪያ ባንትይርጉ ።
፳፺

ለጤናችሁ እጅጉን እንደምን ሰንብታችኋል ። እኔ እንደሰማችሁት ሁሉ እሁ ሰት ላይ ማለትም እግምባሬ ላይና እጉልበቴ ላይ ቆስዬ ወንድሜም ልጅ ኃይለ ማርያም ኮላሴና ብዙም የታመኑ አሽከሮቼ ሲሞቱ እኔ ተርፌ ለሕክምና አዲስ አበባ ሆስፒታል ተኝቼ በሕክምና ላይ ሳለሁ እናንተም ወደዚህ መምጣታችሁን ሰማሁ ። እኔም ምንም እንደወትሮው ጤንነቴ የተስተካከለ ባይሆንም ቁስሌ ጠገን ሲል ብታስወስዱኝ አንድ ሥፍራ ይገኛ ሕይወቴ እስቲያልፍ እምዋጋ ነኝ ።

ይህም የምትሰሙት ድምፅ ባዶ ቅሬንታ ካትሮና ግመልና የኢጣሊያን ምስ ንጅር ብቻ በመሆኑ ተዋጊ ጦር የለውምና በርቱ ። ለጊዜው 30 የሚሆኑ አሽከር ቼንና ሁለት ማለፊያ መትረየስ በእንደራሴዬ በአቶ ንጉሤ አጋዥ እጅ ልኬላችኋ ለሁና በርቱ ።

ፊታውራሪ ኀንጉል ኮላሴ ።

ፊታውራሪ ኀንጉል ኮላሴ ሜኤሶ ላይ በኢጣሊያኖች ተከበው ተያዙ ። ከዚያም ሐረር ከተማ ከሚገኘው እውዚን ከሚባለው ወህኒ ቤት ሶስት ዓመት ከታሰሩ በኋላ በቁም እስር ከከተማ እንዳይወጡ ታግደው ተለቀቁ ። በመጨረሻም በ1947 ዓ.ም ሰኔ 19 በሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሐረር በሚገኘው በጥምቀተ ባህር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

———o———



ጓንጉል ኮላሴ ።



ኃይለማርያም ኮላሴ ።

## የአዲስ አበባ መያዝ

ማርሻል ባዶሊዮ ሚያዝያ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ከጦር መኰንኖቹ ጋር በ12 አይሮፕላኖች ታጅቦ ደሴ ገባ ። ማርሻል ባዶሊዮ ከአዲስ አበባ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ደሴ ላይ ሆኖ ለአዲስ አበባ ጉዞ ዝግጅት ድርግ ጀመር ። የአዲስ አበ ባውን መንገድ የሚጠርግ ቀዳሚ ቡድንም በጀኔራል ዳል አራ የሚመራ አዘጋጀ ። «...እኔ እንድመራው በተደረገው ቀዳሚ ቡድን ዝግጅት ውስጥ 1785 መኪናዎች፣ አንድ የቀላል ታንክ ብርጌድና 11 መድፍ ነበረን ።...» ሲል የቡድኑ መሪ ጀኔ ራል ዳል አራ ጽፎታል ።

ሚያዝያ 16 ቀን በእያንዳንዱ ባታሊዮን አራት ሺ ሰዎች ያሉበት ሁለት የቅኝ ግዛት ወታደሮች ባታሊዮን ለአሰሳ ቀድሞ ወደ አዲስ አበባ ተላኩ ። በሳልስቱ ማለት ሚያዝያ 18 ቀን ጧት 12.495 የኢጣሊያ ወታደሮች በመኪናዎች ተሳፍ ረው ሁለተኛውን ተከታይ ጉዞ ቀጠሉ ። በዚህ በሁለተኛው ተጓዥ መሀል በመ ኪናዎች የተጫኑት ወታደሮች ብቻ ሳይሆኑ ፣ ፈረሶችም ጭምር ነበሩ ። ለአዲስ አበባ አገባብ የወጣው ፕሮግራም ማርሻል ባዶሊዮ አዲስ አበባ ከተማ የሚገባው በፈረሰኞች ታጅቦ ነው ይል ስለነበር ለዚሁ አጀብ የሚሆኑ ከኢጣሊያ የመጡ 193 ምርጥ ፈረሶች በመኪና ተጭነው ተጓዙ ።

መንገዱ ተዘግቶ ማለፊያ እናጣለን ብለው ኢጣሊያኖች የፈሩት የጣርማ በር እንኳ ያለብዙ ጉዳት አሳለፋቸው ። የኢጣሊያ ወታደሮችም ደብረሲና ከደረሱ ጀምሮ«....በሚመለከቱት ነገር ሁሉ ተመሰጡ ። የሚያዩት ሁሉ አስደናቂ ፣ በእር ግጥ አስደናቂ ውበት ነበር ። ክፍት በሆኑት መኪናዎች ላይ ያሉት ሰዎቻችን ጠመ ንጃዎቻቸውን በጉልበቶቻቸው መሀል ይዘው አቧራ በለበሰ ፊታቸው እየተዟዟሩ ያን የደለበ መሬት እያዩ ሲደነቁ «ኖ» በተባለው በጃፓኖች ፊልም ውስጥ የተካ ፈሉትን አክተሮች ይመስሉ ነበር ። በዚያም ሆነ በዚህ የሚታየው ሁሉ ፣ ሀብት ስለሆነ ወታደሮቻችን አይናቸውን አፍጠው የኛ ነው ፣ የኛ ነው ይላሉ ። እህሉ ተዘርቶ ፣ ሰብል ጉብቶና ተሸጦ ገንዘብ አሁኑኑ ያገኙ ይመስል ሁሉም ሚሊዮነር እንደሆኑ አድርገው ይጫወታሉ ። ለፍተን ለፍተን በመጨረሻው እውነተኛ ቅኝ ግዛት አገኘን እያሉ እርስ በርሳቸው ያወራሉ...» በማለት ቶማሲሊ ጽፏል ።

ሚያዝያ 27 ቀን ከሰዓት በኋላ ብረት ለበስ የሆነው የማርሻል ባዶሊዮ ጦር አዲስ አበባ ከተማ ጫፍ ደረሰ ። በአዲስ አበባ ከተማ ኃይለኛ ዝናብ ይዘንባል ። ነጐድጓዱ አዲስ አበባን መድፍ የሚተኮስባት የጦር ሜዳ አስመስሏታል ። ከቀኑ አሥር ሰዓት ሲሆን የኢጣሊያ ጦር አዲስ አበባ ከመግቢያው በር ደረሰ ።

ማርሻል ባዶሊዮ በደመቀ አጀብ ታጅቧል ። በፈረስ ተቀምጠው ዙርያውን ካጀቡትም መሀል ፣ በኋላ የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ የሆነው ጁሴፔ ቦታይ ፣ የቅኝ ግዛት ዋና ፀሐፊ የነበረውና የማርሻል ባዶሊዮ ቹፍ አፍ አስታፍ የሆነው አሌሳ ንድሮ ሌሶና እና ሌሎችም የፋሺስት ሹማምንቶች ነበሩ ። የባዶሊዮ ታማኝ ጀኔ ራሎችም አጅበዋል ።

ሲስኮ ቶማሲሊ ስለዚያች ቀን ጉዞ ሲገልጽ«...ቀበና ካለው የፍተሻ ጣቢያ ማረሻል ባዶሊዮ ሲደርስ በሰልፍ የቆሙ ወታደሮች ለድል አድራጊው ለባዶሊዮ በብረት ሰላምታ ሰጡ ። ወታደሮቹ የያዙት ጠመንጃ የተለያየ ዓይነት ቢሆንም የኢ ጣሊያ ወታደሮች ግን በምርጥ የጦር መሣሪያ ተገቢውን ሰላምታ ሰጡ ። በእያን ዳንዱ ጐጆ ሁሉ ላይ ነጭ ባንዲራ ተሰቅሏል...» ብሏል ።

ባዶሊዮ እንደታጀበ ጥቂት ማይል ያህል ተጓዘ ። ቀበና ጉራንጉር ውስጥ ሲደ ርስ ወደ ቀኝ ታጠፈ ። ከዚያም በባሕር ዛፍ ጫካ ውስጥ ተጉዞ ኢጣሊያ ለጋሲዮን ገባ ። ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን አይሮፕላኖች በአየር ውስጥ እያንዣበቡ በመ ገለባበጥ ትርኢት አሳዩ ። ጆቫኒ አርቴየሪ የተባለው ጋዜጠኛ በመጽሐፉ "...በድ ምፅ ማጉሊያ አቴንሲዮኒ (ፀጥታ) የሚል ድምፅ አራት ጊዜ ተሰማ ። ከዝናቡ በስተ ቀር ሌላው በሙሉ ጭጭ እርጭ አለ ። ዝናቡ ግን በፊት ላይ ፣ በእጅ ላይ ፣ በጠ መንጃ ላይ ፣ በዛፎችና በአበቦች ላይ ሁሉ ይወርዳል ። ሶስት ጊዜ ለንጉሡ ጤን ነት ፣ ሶስት ጊዜ ደግሞ ለሙሶሊኒ ጤንነት ተባለ ። የአየር ማርሻሉ የማሊዩኮ (Magliocco) ፊት በዝናብ ይሁን በእንባ ርሷል ። የባዶሊዮም እንደዚሁ ነው ። ጀኔራሎቹ እርስ በርሳቸው ይጫወቱ ጀመር ። ማርሻል ባዶሊዮ 'አደረግነው ፣ አደረ ግነው ፣ ደህና ሁን አንተ የተከበርክ ጦርነት' አለ ። እኔንም አየና 'ይሄ በጭቃ መከዳ ላይ ከመሬት ተቀምጦ የመጨረሻውን ዜና ታይፕ የሚመታው የእናንተ ጋዜጠኛ ነው' ብሎ ተናገረ ።..." በማለት ጽፏል ።

ጋዜጠኛው ጆቫኒ አርቴየሪ ጭቃውን ሳይጠየፍ ጭቃ ላይ ተቀምጦ የገፈው ዜና ኢጣሊያ አገር የደረሰው ዘግይቶ ነው ። ዜናው ሮማ ከተማ የተሰማው ሌሊት ነው ። "ማረሻል ባዶሊዮ አዲስ አበባን ያዘ" የሚለው ዜና ሮማ ውስጥ ሲነዛ ሕዝቡ ግልብጥ ብሎ ወጣ ። መንገዱ ሁሉ በሰው ተሞላ ። ፒያዛ ቬኒዚያ የተባለው የሙ ሶሊኒ ዲስኩር መናገሪያ አደባባይ ጥቅጥቅ ብሎ በሰው ተያዘ ። ሙሶሊኒም ከተለ መደው ባልኮኒው ላይ ቆመ ። ሪስፖሊ የሙሶሊኒን ንግግር እንደጻፈው "......ባለ ፈው በ3000 ዓመታት ታሪካችን ውስጥ ኢጣሊያ አኩሪና ታሪካዊ ሥራዎችን ሠር ታለች ። ይህ የዛሬው ግን ምንም የማያጠያይቅ ከሁሉ የበለጠ ታሪካዊ ሥራ ነው። ለዘለዓለምም ሲታወስ የሚኖር ታሪካዊ ተግባር ነው ። የኢጣሊያ ሕዝብ ሆይ ! የዓ ለምም ሕዝብ ሆይ ! የሰላም መሠረት ዛሬ ተጣለ..." ሲል ንግግር አደረገ ። ሙሶ ሊኒ ንግግሩን ጨርሶ ሊሄድ ሲል ሕዝቡ አቆየው ። ሕዝቡ ሙሶሊኒ ወደቆመበት ሠገነት እጁን በማርገብገብና በመጮህ እንዳይሄድ ለመነው ። በተለይ ወጣቶች የፋ ሺስትን መዝሙር እየዘመሩ ዱቼ ሙሶሊኒን እንዳይሄድ አደረጉት ።

ይህ ከሆነ ከሁለት ቀናት በኋላ የኢጣሊያኑ ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል 3ኛ ፣ ታላቁን የሳቮያ ኒሻን ለሙሶሊኒ ሸለሙ ። በሽልማቱም ሥነ ሥርዓት ላይ "...እንደ ጦር ሚኒስትርነቱ ፕላኑን አዘጋጀ ። መራ ። በቅኝ ግዛቶች ታሪክ ውስጥ ታላቅ የሆ ነውን ጦርነት ድል አደረገ ።....... ይህ ድል ለፋሺስት አገራችን ታላቅ ኩራት ነው ......." ሲሉ ንጉሡ ነገሥት ቪክቶር አማኑኤል ንግግር አደረጉ ።

ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ሙሶሊኒ "...የኢጣሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ድል አድርጐ ይዟል ። ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቄሳር ግዛት መሆንዋን ለዓለም እናሳውቃለን..." በማለት አወጀ ። አራት አገሮች ብቻ የኢጣሊያን ገዢ ነት እናውቅም አሉ ። እነሱም አሜሪካ ፣ ሶቪየት ሕብረት ፣ ሜክሲኮና ኒውዚላንድ ናቸው ።

ማረሻል ባዶሊዮ አዲስ አበባ ከገባ ከሶስት ቀናት በኋላ አዲስ አበባ ከተማ ሕይወት መዝራት ጀመረች ። ወደ እንጦጦ ተራራ ሸሽተው የነበሩ አምሳ ሺ ያህል ሰዎች ወደ ቤታቸው ተመለሱ ። ሬሳው ሁሉ እየተጠረገ ከተማይቱ ፀዳች ። እን ጂሎ ዴል ቦካ እንደ ፃፈው"....ሳኬሪላሪስ የተባለው ጠጉር ቆራጭም ከዘራፊዎች የተረፈችውን እንዲት መስተዋት ይዞ ሱቁን ከፈተ..." ብሏል ።

ቦታይ (Bottai) የአዲስ አበባ ከተማ ገዥ ተብሎ ተሾመ ። ቢሮውንም ዛሬ ዩኒቨርስቲ ከሆነው ከድሮው ግቢ አደረገ ። በዚያ ግቢ ውስጥ የነበሩትንም ስድ ስት አንበሶች እንዲገደሉ አዘዘ ። የዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ ሰላም ሆና ሰላማዊ


ትምበል እንደ በኢጣሊያኖች ዘንድ ፍርሐት ስላለ 426 መኰንኖች ያሉበት 9934 ወታደሮች የሚጠብቁት ነበሩ ።

ማርሻል ባዶሊዮ ለአስራ አምስት ቀናት ያህል አዲስ አበባ ቆይቶ ግንቦት 14 ቀን ወደ ሮማ ተመለሰ ። በሱም ቦታ ጀኔራል ሮዶልፍ ግራዚያኒ ጥብቅ ገዥ ተብሎ ተሾመ ።


በ1928 ዓ.ም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር ባሰለፈችው ጦር ያወጣችው ወጭ ቀላል አልነበረም ። ከደረሰባት የሰው እልቂት ሌላ 12 ሚሊያርድ 111 ሚሊዮን ሊሬ ለጦርነቱ ወጭ አድርጋለች ።



ፈረሶች ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ ።



ፈረሶች ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ ።



አዲስ አበባ ከተማ በኢጣሊያኖች በተያዘች ጊዜ ።

# ፲፱፻፳፰

ማረሻል ባዶሊዮ በታላቅ ሰልፍ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ ገባ ። በኢጣሊያ አገርም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ የገባው ኢጣሊያዊ የሆነና የኢጣሊያ ተከታይ ሁሉ ኢትዮጵያ የኢጣሊያን አገዛዝ በሰላም የተቀበለች አድርጐ አመነ።

ካኒቫሪና አንዳንድ ምሁራን ብቻ "....ይህ ነገር አላማረንም..." ይሉ ጀመረ ። ካኒቫሪ በታሪክ መጽሐፉ ሲገልፀውም "....ይህ ነገር አላማረኝም ። ሕዝቡ ሁሉ ተደስቷል ። ወደፊትም ታላቅ ደስታ እንደሚጠብቀው ይታየዋል ። እኔን የሚታየኝ ግን ተቃራኒው ነው ። እያንዳንዱን ነገር ሳስባት መዘዝዋ እጅግ በጣም የከፋ ይሆንብኛል ። ዋናዋ ከተማ ራስዋ በብዙ ባህር ዛፎች የተሸፈነች ደን ነች ። በዚህ ደን ውስጥ ያለው የኛ ሕዝብ 7200 ነው ። ይህ የኛ ሰው ዙሪያውን ተከቧል ። ከተማዋን የከበብዋት ሰዎች አንድ መቶ ሺህ ይሆናሉ ።...የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ኢጣሊያን በሚያስጠላ መጥፎ ፕሮፓጋንዳ ተበክሏል ።... አገሪቱ ውስጥ ብዙ የጦር መሳሪያ አለ ። በዚያ ላይ ደግሞ የእንግሊዝ ግዛት ከሆኑት ጐረቤት አገሮች የጦር መሣሪያ ንግድ ተሟሙቆ በገፍ ይገባል ። እርግጥ የኛ ሰዎች የጦር መሣሪያ እንዳይገባ ከአገሪቱ ወሰን በጣም ጥቂቱን ክፍል ብቻ ይቆጣጠራሉ ። ደግሞም የክረምቱ ወራት ለመግባት ተቃርቧል ። በዚያን ጊዜም ጦራችንን ለማጠናከርም ሆነ ስንቅ ለማግኘት ፈጽሞ የማይቻል ነው ። ...." በማለት የያዘውን ማስታወሻ በኋላ ባሳተመው መጽሐፉ ላይ አትሞታል ።

ማረሻል ባዶሊዮ እንደፃፈው "......እስከ ግንቦት አንድ ቀን ድረስ በአዲስ አበባና በአካባቢዋ ያለው ሕዝብ 3500 ጠመንጃ ፥ 89 ሽጉጥ ፥ 35 መትረየስ ፥ ሁለት መድፍና በርከት ያሉ ጥይቶችን አስረከበ ።..." ይህ ከሆነ በኋላ በቀጠለው ሳምንት ደግሞ ማለት ግንቦት 7 ቀን ድረስ 7,853 ጠመንጃዎች ፥ 80 ሽጉጦች ፥ 156 መትረየሶችና 51 መድፎችን አስረከበ ።

ይህን መሣሪያ ከአዲስ አበባና ካካባቢዋ የተረከበው የፋሺስት መንግሥት ኢትዮጵያውያን አጠቃለው የጦር መሣሪያቸውን ያለማስረከባቸውን ቢያውቅም ውዴታ ቀርቶ በግዴታ እንዲሠራ ግንቦት 5 ቀን 1928 ዓ.ም ሙሶሊኒ ለግራዚያኒ "...እንኚህን ወጣት የሚባሉትን ኢትዮጵያውያን ጨርሳቸው ።..." የሚል ትእዛዝ አሳለፉ ። ሙሶሊኒም ይህን ትእዛዝ ያሳለፉበት ምክንያት በሸዋ የመጀመሪያው አርበኛ የሆኑት ወጣቱ ልጅ ኃይለማርያም ማሞ ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም የኢጣሊያ ሠራዊት ከደሴ ወደ አዲስ አበባ በሚጓዝበት ጊዜ ደብረ ብርሃን አካባቢ ላይ ተኩስ ከፍተው ገጥመውት ስለነበር ነው ።

የሙሶሊኒ ትእዛዝ ከደረሰ ከአስር ቀናት በኋላ ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛት ሚኒስትር ለሌሶና ባስተላለፉት ቴሌግራም "....ትናንት ከሰዓት በኋላ (እ.ኤ.አ. ግንቦት 13 ቀን) የመንገድ ሥራ ቡድናችን የጂጂጋ ሐረርን መንገድ በሚሠራበት ጊዜ ከጂጂጋ 34 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ጦር መሣሪያ በያዙ አበሾች ተጠቅተው ነበር ። ወዲያውኑም አጥቂዎች ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ተመልሰዋል ። ...ትእዛዜና መልእክቴ በአይሮፕላንና በእግረኛም እንዲደርስ አድርጌአለሁ ። በብዛት ላሉም ሆነ ለግለሰቦች ሁሉ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት መውደቁን እንዲያውቁት ነግሬአለሁ ። ይህን ትላልፎ ከኛ ወታደሮች ወይም ሰዎች ጋር ግጭት የሚፈጥር ቢገኝ እንደሽፍታ እንደሚቆጠርና አስፈላጊው መልስ የሚሰጠው መሆኑን እንዲያውቁት አስጠንቅ

ቁአለሁ ። ...በእንዲህ ዓይነቱ የተያዙ እስረኞችም በእስቸኳይ እንዲገደሉ አዝዣለሁ ። ሽማምንቱና ሌላውም ሕዝብ በሽፍትነት ተግባር እንዳይሰማራና ቢሰማራ ግን ከባድ ቅጣት እንደሚቀጣ የሚገልፀውን አዋጅ በአይሮፕላን በአግረኛም በትኛለሁ ።......" ብሏል ።

ሰኔ 4 ቀን 1928 ዓ.ም ግራዚያኒ ቬቼሬ ዲ. ኢትዮፒያ ተብሎ በሙሶሊኒ እንደ ተሾመ አዲስ አበባ ውስጥ ኢትዮጵያውያንን ሰብስቦ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ! የኢጣሊያው ንጉሥ የኢትዮጵያ ቄሣር እኔን ወደዚህ የላኩኝ ግዛታቸውን በጥሩ ሁኔታ እንድጠብቅ ነው ። ታላቁ ሙሶሊኒ የኢጣሊያው ፋሺስት ዱቼ አገሪቱ ወደ ነበረችበት ሰላም ተመልሳ እንድትረጋጋ እንዳደርግ አዘውኛል ። መጥፎ ሰዎች የሚነዙትን የሀሰት ወሬ አትስሙ ። አሁን ኢጣሊያ የመላው ኢትዮጵያ የበላይ ናት ። ስለዚህ የወጣው ወጭ ቢወጣም አገሪቱን ሰላም ማድረግ ቀደምት ተግባራችን ስለሆነ አሁን በፊቴ ያላችሁ መኳንንትና ሕዝብ ሁሉ ፤ አሉ የሚባሉትን ሽፍቶች በሰላም እንዲገቡ ምከሩዋቸው ። እጃቸውን ይስጡ ። ባይሰጡ ከባድና ከፍተኛ የሆነ ቅጣት ይቀጣሉ ። ገበሬዎች እረሱ ፣ ነጋዴዎችም ነግዱ ። የታላቁን የዱቼን ቃላት ብታዳምጡ መላው ግዛት ከዳር እስከዳር ይለማል ። ይበለጽጋል ። በሌላው በኩል ደግሞ ሽፍቶች እይቀጡ ቅጣት እየተቀጡ ይደመሰሳሉ ፣ ጨርሰውም ይጠፋሉ" በማለት ንግግር አደረገ ።

ከባድ ችግር የፈጠረው ከአዲስ አበባ ደሴ ያለው መንገድ ነበር ። ይህ መንገድ ቢዘጋ ኤርትራ ካለው የስንቅና ትጥቅ ማከማቻ ጋር ግንኙነታቸው እንደሚቋረጥ ስለሚያውቁ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም በደብረ ብርሃን እና በደብረ ሲና ያለውን ኃይላቸውን በአጠፌታ አጠናከሩ ። የአርበኞች መከማቻ ይሆናል ተብሎ የተጠረጠረው አንኮበር ከተማ ግንባት 21 ቀን ሲያዝ 447 ጠመንጃ ፤ 20.000 ጥይት ፣ አራት መትረየስና 170 የመድፍ የተለያየ ክፍል ለኢጣሊያ ገባ ። በግራዚያኒ አሠራር የተደሰቱት ሙሶሊኒም ግንቦት 28 ቀን ለግራዚያኒ "....የተያዙት እስረኞቹ ሽፍቶች በሙሉ መገደል አለባቸው" የሚል ቴሌግራም አስተላለፉ ።

በሰኔ ወር የክረምት ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ኢጣሊያኖች ከገቡበት ቦታ መንቀሳቀስ አቃታቸው ። በዚህ ጊዜ አርበኞች እየተበራቱና እየተሰበሰቡ በዝተው የሽምቅ ውጊያቸውን ቀጠሉ ። ሰኔ 6 ቀን በኢትዮጵያ አርበኞች በአቃቂና በሞጆ መሀል ያለው የስልክ መስመር ተበጣጥሶ የባቡሩ ሐዲድም ተሰባበረ ። በዚህም ምክንያት ኮራዶ ዞሊ እንደገለፀው«....ትራፊኩ ለስምንት ቀን ተዘጋ ።....»

የባቡሩ ሐዲድ ተጠግኖ ሥራ ቢጀመረ በጥቂት ቀን ውስጥ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በባቡር የመጣው ኢቭሊን ዋህ በጉዞው ያየውን ሲጽፍ ።«..... የተፏፏቀ ውጊያ አለ ። ባቡሩ የሚጓዘው በቀስታና መንገዱን እየፈተሸ ነው ። ሁለት ድልድዮች ተሰብረው ጥገናው አንድ ቀን ተኩል ፈጅቷል ።....መትረየስ ተኳሾች ባቡሩን ይጠብቃሉ ። እነዚህም መትረየስ ተኳሾች ከባቡሩ ፊትና በኋላው ሆነው ይጓዛሉ ።....» ብሏል ። በባቡሩ መስመር ላይ በየጊዜው የደረሰው አደጋ ብዙ በመሆኑ ለብቻው ጽፌዋለሁ ።

የኢጣሊያ አየር ኃይል አዛዥ ማረሻል ማሊዮኮ በሶስት አይሮፕላኖች ከተከታዮቹ ጋር ሆኖ ወደ ወለጋ ተጓዘ ። ሰኔ 20 ቀን ከለቀምት ከተማ አይሮፕላኖቹ እንዳረፉ 300 ያህል የሚሆኑ በሆለታ ጦር ትምህርት ቤት የነበሩ ወጣቶች ተኩስ ከፍተው በተደረገው ውጊያ ማረሻል ሚሊዮኮ እና 11 የኢጣሊያ መኰንኖች ተገደሉ ። ይህም በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደተሰማ ሌላ ድንጋጤን ፈጠረ ።

ሐምሌ 2 ቀን ናዝሬት የሠፈረውን የኢጣሊያ ጦር አርበኞቹ መቱት ። እንደ ላንዲ እና እንደ ዞሊ አፃፃፍ«......ብዙ ኢጣሊያውያንና አንጋፋው ጦር መሪ ጀኔራል ሜርካቲ በከባዱ ውጊያ ተገደሉ ።....» ሐምሌ 12 ቀን በደብረ ብርሃንና

በኮረማሽ በተደረገው ወጊያ አርበኞች አሸንፈው በየከተማዎቹ ገቡ ። ሐምሌ 14 ቀንና 15 ቀን እንኮበር ከተማ በአርበኞቹ መያዙን ዞሊ ጽፏል ።

አዲስ አበባ ከተማን ለመውረርና ኢጣሊያን ከአዲስ አበባ ለማስወጣት አርበኞች አምስት ቀናት የፈጀ ስብሰባ አደረጉ ። ስብሰባው የተደረገበት ዋናው ምክንያት ፤ ወታደር ያለው መኳንንት ሁሉ በየርስቱ ላይ ሆኖ የርስት አገሩን ብቻ ላለማስነካት ስለ ወሰን እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ እንዲቀርና ማንኛውም ሰው ለርስቱ ሳይሆን ለኢትዮጵያ እንዲዋጋ ለማድረግ ነበር ። በዚህ በኩል ከስምምነት ከተደረሰ በኋላ የአገር ክፍፍል ተደረገ ። በክፍፍሉም መሠረት ደጃች ባልቻ በጉራጌ ፣ ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያት በሊሙ ፣ ባላምበራስ አበበ አረጋይ በጊዳ ፣ ደጃዝማች ዘውዱ አስፋው በሙሎ እንዲሆኑ የሸዋ አርበኞች ሸዋን ተከፋፈሉ ። ከዚያም በፊት ራስ እምሩ በወለጋ ሲገኙ ራስ ደስታ ደግሞ ሲዳሞ ውስጥ ነበሩ ።

ይህ ድልድል ከተከናወነ በኋላ ደጃዝማች አበራ ካሣ ሐምሌ 21 ቀን 1928 ዓም አዲስ አበባ ከተማን ወርረው ኢጣሊያን ለማስወጣት አሰቡ ። በተናጠል የማይመች መሆኑም ስለታወቀ በሕብረት ለመሥራት ተወስኖ ባላምበራስ አበበ አረጋይ በቀበና እቦ በኩል ፣ ደጃዝማች አበራ ከሰላሌ ተነስተው በእንጦጦ በኩል ፣ ደጃዝማች ዘውዴ አስፋው በሆለታ በኩል ፣ ደጃዝማች ባልቻ በልደታ ቤተ ክርስቲያን በኩል ፣ ደጃዝማች ፍቅረማርያም በኡራኤል በኩል ዙሪያውን እንዲያጠቁ ሆኖ ከበባውም ሐምሌ 20 ቀን እንዲሆን ተወሰነ ።

ውሳኔው ይወሰን እንጂ ልክ እንደተወሰነው በተወሰነው ጊዜ ከባቢው ሥራዊት ሊገኝ አልቻለም ። ያልተገኘበትም ዋናው ምክንያት የሐምሌ ዝናብ እያየለ ስለሄደና ወንዞቹ ስለሞሉ መሻገሪያ በማጣቱ ነው ። ደጃዝማች አበራ ካሣ በጉለሌ በኩል ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ድረስ መጡ ። ከዚያም ሆነው ምልክት የሚሰጥ ምንም የተኩስ ድምፅ በማጣታቸው ለመመለስ ቆረጡ ። አጠገባቸው የነበሩት ደጃዝማች ዘውዴ አባኮራን ግን እኛው ብቻችንን አዲስ አበባ ገብተን ከኢጣሊያ ጋር እንግጠም ብለው ወደከተማዋ ጦሩ ሲያመራ ኢጣሊያኖች ምሽግ ገብተው ተኩስ ከፍተው መለሱዋቸው ። በዚህ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ የአርበኞቹን መጠጋት ሰምቶ ስለነበር የተኩስ ድምፅ ሲሰማ የከተማው ሕዝብም ይተኩስ ጀመር።

ማርያ ጂያኮኒያ ላንዲ የተባለች ኢጣሊያዊት ነርስ በያዘችው ማስታወሻ «...ሐምሌ 20 ቀን (በኛ ሐምሌ 13) በአዲስ አበባ ከተማና በአካባቢው ሲተኮስ አደረ ። በሐምሌ 21 ቀን የሽፍቶቹ ኃይል አዲስ አበባን መክበቡ ተነገረን ። የአዲስ አበባ ከተማን የከበበው የሽፍታ ብዛትም 40.000 እንደሚሆን ይወራል ። ሐምሌ 22 ዶክተር ቦራ የሚያክምበት ጉለሌ መንገድ ላይ ያለው የኢጣሊያኖች ሆስፒታል እንዲዘጋና ከአሮጌው ምኒሊክ ሆስፒታል ጋር ተደርቦ እንዲሠራ ተወሰነ ። ምክንያቱም ይህ ሆስፒታል ለሽፍቶቹ የተጋለጠና አደገኛ ቦታ ላይ ስለሆነ ነው ።...» ብላለች ።

ሐምሌ 21 ቀን አዲስ አበባ ከተማ በአርበኞቹ ተጠቃች ። ዞሊ ስለዚያን ዕለቱ ሁኔታ ሲገልጽ «..... በጥሩ ኃይል የተጠናከረ የነዋሪዎቹና የሽፍቶች ኃይል ነበር ። ሽፍቶቹ የሚመሩት በአበራ ካሣና በደጃዝማች ባልቻ ነበር ። ...» ሲል ቦላቲም ይህንኑ የአርበኞቹን ጠንካራነት መስክሯል ። ላንዲ ደግሞ «.....በአበራ ካሣ የሚመራው ሽፍታ 30.000 ነው ። እነኚህም ሽፍቶች በአዲስ አበባ ከተማ ዙርያ ባሉት ደኖች ውስጥ ናቸው ። አላባቸውም ከተማዋን ለመያዝ ነው ። የኢጣሊያን ሆስፒታል አጥቅተዋል ። ከዚያም አልፈው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ተኩስ ተታኩሰዋል.....» ብላለች ። የላንዲን ማስታወሻ ለማጠናከር ዋህ ደግሞ በመጽሐፉ «... ሽፍቶቹ ፣ መሀል ከተማው ድረስ ገብተው ተታኮሱ ። ከአዲስ አበባ ከተማ ተባርረው እስኪወጡም ድረስ ብዙ ሰው ገድለው ከተማዋንም ዘርፈዋል ።...» ሲል ጽፏል ።

ሐምሌ 22 ቀን ስለነበረው ሁኔታ ፖሊ ሲገልጽ«....አይሮፕላኖች ተነስተው በአዲስ አበባ ከተማ ዙርያ እየዞሩ ሽፍቶቹን በቦምብና በመትረየስ ሲደበድቡ ዋሉ። በመጨረሻም ሽፍቶቹን አባረሩዋቸው።.....» ሲል ላንዲ ደግሞ«.....ከአዲሱ ቤተ መንግሥት (ዛሬ ዩኒቨርስቲ) በላይ ያለው ተራራ በሙሉ በሽፍቶች ተይዟል።...» ብላለች ።

ከአርበኞቹ ጋር የመጡት አቡነ ጴጥሮስም ሐምሌ 22 ቀን ተገደሉ ። የእሳቸውንም መገደል በቴሌግራም ቁጥር 1645/8837 «....አቡነ ጴጥሮስ ሐምሌ 29 ቀን ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት በጥይት ተደበደቡ።.....» በማለት ግራዚያኒ ወደ[6] ሮም ካስታወቀ በኋላ በማግሥቱ ሐምሌ 23 ቀን በቴሌግራም ቁጥር 1667/8906 ደግሞ «.....አቡነ ጴጥሮስ ሕዝቡንና መኳንንቱን በስብከት ከሚያሸብሩት አራት ጳጳሳት አንዱ ነበር። ስለዚህ ተገደለ።» ሲል ለቅኝ ግዛት አገሮች ሚኒስትር አስተላለፈ። የአቡነ ጴጥሮስ አሟሟት ለብቻው ተተርኳል ።

ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አባተጫን እስከ እንግሊዝ ኤምባሲ ድረስ ሲገቡ፣ ደጃዝማች ባልቻ ደግሞ እስከ ዛሬው አሮጌው አይሮፕላን ማረፊያ ድረስ ገብተው ነበር። ነገር ግን ዝግጅቱ አልባባ ስላለ ሁሉም በየአቅጣጫው ተኩስ ቢከፍትም እየተሸነፈ ተመለሰ። የደጃዝማች አበራ ካሣ ሠራዊትም ሐምሌ 22 ቀን ወደ መጣበት ወደ ሰላሌ ሄደ ።

በዚህ ጊዜ ለሸዋ አርበኞች እንደታላቅ መሪ የሚቆጠሩት ደጃዝማች አበራ ካሣ ነበሩ ። ደጃች አበራ ካሣ ሀብትም ሆነ ብዙ ሠራዊት ስለነበራቸው ዙርያቸውን ካሉት አርበኞች ሁሉ እሳቸው ላቅ ያሉ ነበሩ ። ለልዑልነታቸው ምልክትም ቀይ ጥላ ያሲይዙ ስለነበር ተራው አርበኛ ሁሉ ወደእሳቸው ተጠጋ ። ሌሎቹም የአርበኞች መሪዎች ቢሆኑ አዲስ አበባን ለማጥቃት ከመወሰኑ በፊት የሁሉም አርበኞች መሪ እንዲሆኑ ደጃች አበራ ካሣን መርጠዋቸው ነበር ። ደጃዝማች አበራ ካሣ ግን የኢጣሊያን ሁኔታ አይተው እጃቸውን ለመስጠት በሚስጢር ከኢጣሊያኖች ጋር መላላክ ጀመሩ ።

ደጃዝማች አበራ ለኢጣሊያ እጃቸውን ለመስጠት መወሰናቸውን የሰማው ሠራዊታቸው ገነገነ ። በተለይም በምርኮኛነት ተይዘው የነበሩትን ስድስት ኢጣሊያኖች ለግራዚያኒ በሰላም በማስረከባቸው ከፍተኛ ብጥብጥና መከፋፈል ተፈጠረ። ደጃዝማችም ሠራዊታቸውን ሰብስበው «.....ኢጣሊያን መዋጋት የምንችለው አሁን አይደለም ። መጀመሪያ መዘጋጀት አለብን ። በቅሎና ፈረስ ፣ ምግብና የጦር መሣሪያ መግዛት አለብን ። እንዲህ ሆነን ከተደራጀን በኋላ እንገጥመዋለን።...» በማለት ተናገሩ ። ምንም እንኳ ደጃዝማች አበራ ይህን በመሰለ ንግግር ደጋግመው ሕዝቡን ቢሰብኩም እየከዳቸው የሚሄደው ሠራዊት ከዕለት ወደዕለት እየበዛ ሄደ። ደጃዝማች ኃይለማርያም ማሞ ተለይተው ወደ ሙገር ሲሄዱ ራስ አበበ አረጋይ ደግሞ ወደ ጅሩ ተሻገሩ ። ደጃች ዘውዴ አስፋውም ተለይተው ወደጉጃም ሄዱ ። ደጃዝማች አበራ ካሣም ከግራዚያኒ ጋር በደብዳቤ መላላካቸውን ቀጠሉ ።

ይድረስ እጅግ የተከበሩ ማርሻል ግራዚያኒ ።

ሰላም ጤንነት ክብርና ምስጋና ለእርስዎ ይሁን ። ይህን ከዚህ በታች የጻፍኩትን እንዲመለከቱልኝ እለምናለሁ ። ክብር ሆይ ፣ ማርሻል ባዶሊዮ አዲስ አበባ የገቡ ጊዜ በሙሴ ባሳሊአስ ዲያማድሬ በኩል ሰላማዊ ሰው መሆኔን በደብዳቤ ጽፌ ልኬ ነበር ። ነገር ግን ማርሻል ባዶሊዮ ለደብዳቤዬ መልስ ከመስጠታቸው በፊት ወደ አገራቸው ሄዱ ። እርስዎም አዲስ አበባ እንደገቡ ያንኑ የመሰለ ደብዳቤ ጽፌ በራስ ኃይሉና በሙሴ ባስሊውስ በኩል ልኬ ነበር ። ለዚህም ደብዳቤዬ መልስ ሳላገኝ

ኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ከአየር በቦምብ አገራችንን መደብደብ ጀመረ ። ባላገሮችንም እየያዘ ችሎት ሆና ፍርድ ሳይታይ በሞት ይቀጣ ጀመረ ።

«እግዚአብሔር ፈቃዱ እስከሆነ ድረስ ማንም ሰው ለአገሩ መዋጋት በዓለም ያለ ልማድ ነው ። ይህን የሚያውቀው ኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ለአገራችሁ ተዋግታችሁ ነበር በማለት ያለ ፍርድ ሰውን መግደሉ አግባብ አይደለም ። አሁንም የእርስዎ ደብዳቤ ሐምሌ 21 ቀን ከደረሰኝ ወዲህ በማግሥቱ ከሐምሌ 22 ቀን ጀምሮ ውጊያውን አቁሜአለሁ ። በደብዳቤዎ መሠረት ባለፈው ሥራዬ ይቅርታ እየጠየቅሁ ከኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ጋር ሰላማዊነቴን አመሠርታለሁ። ለኔም ሆነ ዙርያችንን ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ይቅርታ እንዲያደርጉልን እለምናለሁ።
ሐምሌ 24 ቀን 1928 ዓም

ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ
ደጃዝማች አበራ ካሣ

ይህ የሁለቱ ወንድማማቾች ደብዳቤ ለግራዚያኒ ከተላከ በኋላ ደጃዝማች አበራ ካሣ በዙርያቸው ካሉት አርበኞች ጋር ከረምቱ እንዳለፈ ደብዳቤ ይፃፉ ጀመር ። የሁለቱ ወንድማማቾች ስም አብሮ ይጻፍ እንጂ ደጃች አስፋ ወሰን ካሣ ግን አብረው አልነበሩም ። ይህንንም ቆየት ብለን እናየዋለን ።

ነሐሴ 10 ቀን ስለነበረው የአዲስ አበባ ሁኔታ ላንዲ በያዘችው ማስታወሻ "………የሽፍቶቹ ስጋት አለ ። የማስጠንቀቂያ አላርም ተነፋ ። ሽፍቶቹ መምጣታቸውም ተነገረን ። 11,000 ወታደሮቻቸውን እየመሩ ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸው ተነገረንና እንድንጠነቀቅ ታዘዝን ።……" ብላለች ። ስለ ነሐሴ 20 ቀን ሁኔታ በጻፈችው ማስታወሻ "……ሽፍቶቹ አዲስ አበባ ከተማን ሊይዙ ተዘጋጅተዋል አሉን ። የመጡትም አምስት የሽፍታ መሪዎች ናቸው ። እያንዳንዳቸውም ከአሥር እስከ 12,000 ወታደሮች እንዳሉዋቸው ተነገረን ። እነኚህም ሁሉ ባንድነት ሁነው እሳባቸው ከተማዋን ለመያዝ ነው ። አንደኛው የሽፍቶች ቡድን በብዙ ሺ ወታደሮች ተጠናክሮ አይሮፕላን ማረፊያው አጠገብ ሠፍሯል ። ይህም በደጃዝማች ባልቻ የሚመራው ቡድን በዚህ ቀን ማታ አዲስ አበባ ከተማን ይይዛል ተባለና የማስጠንቀቂያ አላርም ተነፋ ። የሰዓት እላፊም ታወጀ ። እንደተባለውም አልቀረ ፣ የደጃዝማች ባልቻ ጦር በዚያ ሌሊት ጉዳት አደረሰ ።… " ብላለች ። ዋህ ስለ ዚያች ዕለት ሁኔታ ሲገልጽ "…..ከድሬዳዋ የተነሱ አይሮፕላኖች መጥተው እነኚያን ሽፍቶች ደበደቡዋቸው ። ከባድ ጦርነት ነበር ። …" ብሏል ።

በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ጩርጩር ውስጥ የአርበኞች ኃይል ቢጠናከርም እንደ ጆሊ አገላለጽ "…..ሕዝቡ 24 መትረየስ ፣ 320 መውዜር ጠመንጃና 1100 የተለያዩ ጠመንጃዎችን ለኢጣሊያ አስረከበ ።…… ከዚህ በኋላ የኢጣሊያኖች እርምጃ ቀጠለ ።……" ነሐሴ 8 እና ነሐሴ 13 ቀናት ቁሉቢ ከተማ በተደረገው ታላቅ ጦርነት አርበኞቹ ድል አድርገው የቁሉቢ ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን በእጃቸው አገቡ ።

ጳጉሜ 5 ቀን ግራዚያኒ "…..በላስታ ያሉ አርበኞች በሙሉ እንዲደበደቡ ። ምሕረት አያስፈልግም ። ታማኞቻችን መስለው የሚለማመጡትን ሁሉ አትስሙዋቸው ። ቀሳውስቱ ሁሉ ያለ ምርጫ እንዲሞቱ አዝዣለሁ ። ላስታ የወንድማማቾቹ የካሣ ልጆች መሸፈቻ ሆነዋልና መንደሮችና ጫካዎች ሁሉ መመታት አለባቸው ።….. አሁን ጊዜው ዝናባማ በመሆኑ እግረኛን ጦር ማንቀሳቀስ ስለሚያስቸግር በአይሮፕላን በቦምብ እንዲደበደብና የመርዝ ጋዝ እንዲረጭበት አስታውቃለሁ ።………" በማለት አዘዘ ። ከዚህ ትእዛዝ በኋላ ወደሮም ባስተላለፈው

ቴሌግራም "…. ዛሬ ጧት ተነስተው የነበሩት ሰባት አይሮፕላኖች የተላኩበትን ጉዳይ ፈጽመው በደህና ተመልሰዋል ። እንደገና ደግሞ….ነገ ጧት አስመራ ያሉ አይሮፕላኖች በሙሉ ተነስተው በቦምብና በመርዝ ጋዝ በአራት አቅጣጫ ሳሊበ ላንና ብልብላ ጊዮርጊስን ጨምረው እንዲደበድቡ አዝዣለሁ……" አለ ።

በሌላው የቴሌግራም ትእዛዙም "……ማንኛውም ሹም የተባለ ሁሉ መሣ ሪያውን እንዲያስረክብ ይሁን ።……….ትልቅም ሆነ ትንሽ ባዶ እንዲሆን ያስፈ ልጋል ።………ይህ ነገር ሊገባችሁ ያስፈልጋል ።……….እስካሁን ባገኘነው ጥናት በተለይ የሸዋ ሕዝብ እየተደጋገመ በቦምብ እንዲደበደብ ይሁን ።………" የሚ ለውን ቴሌግራም ለመላው ኢጣሊያ ሹማምንት አስተላለፈ ።

ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያ ኒውስ በተባለው መጽሔት ላይ ሳቫ እንደጻ ፋት "……….በዚህ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ የፋሺስት ወታደሮች ባንድ ጊዜ ባንድ መደዳ አሥር ሰዎችን መስቀል የሚችል እንጨት ሠሩ ።……….."ብሏል። ይህ የተባለው የሰው መስቀያ ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ ሁለት ሜትር ተኩል ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ገበያ ውስጥ የተሠራው የሰው መስቀያ በእ ንጨት ተራና ማር ተራ መሐል ነበር ። በመስቀያው ግራና ቀኝም ከፍተኛ ብርሃን የሚ ሰጥ ኤሌትሪክ ተደርጐ የተሰቀሉ ሰዎች ሬሳ ለሊቱን ሁሉ በጥሩ ሁኔታ ይታይ ነበር ። አንዳንዴ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ ሁለት ቀንና ሁለት ሌሊት በዘብ እየተ ጠበቀ ይቆይ ነበር ። እ.ኤ.አ. ነሐሴ 27 ቀን 1938 ዓ.ም. የወጣው ዊክሊ ኢሉ ስትሬትድ የተባለው ጋዜጣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ስለሚሰቀሉት ሰዎች ሲያ ትት "….በአዲስ አበባ ከተማ በየቦታው ሰዎች ይሰቀላሉ ። በተለይ በአዲሱ መስ ቀያ ሰዎች ሲሰቀሉ ለሌላው ተመልካች ማስጠንቀቂያ እንዲሆን ከተሰቃዮቹ የተገ ኘው የጦር መሣሪያ አብሯቸው ይሰቀላል….." ብሏል ።



# አቡነ ጴጥሮስ

አቡነ ጴጥሮስ በ1928 ዓ.ም. ሐምሌ 22 ቀን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በፋሺስት የተገደሉ ጳጳስ ናቸው ። አቡነ ጴጥሮስ የምስራቅ ኢትዮጵያ ጳጳስ ነበሩ ። በ1923 ዓ.ም. ጥር 23 ቀን በወጣው የጳጳሳት ድልድል ለአቡነ ጴጥሮስ የተሰጠው አገር "ከበሸሎ በመለስ አባይ ፈረን ሳይ ቅኝ ግዛት ወሰን ድረስ" ይላል ። ይህንንም የድል ድል ቦታ ሲተነትን የአቡነ ጴጥሮስ የአስተዳደር አገር መንዝ ፣ ግሼ ፣ ወረይሉ ፣ ጃማ ፣ ቦረና ፣ ደራ ፣ ይፍራታ ፣ አንጾኪያ ፣ ግድም ፣ ሳይንት ፣ አምባሰል ፣ ወረሂመኖ ፣ ወረባቡ ፣ ወረቤች ፣ ወረዋዩ ፣ ተኩለደሬ ፣ ወረቃሉ ፣ አባይቤት ፣ ጨረቻ ፣ ለጋምቦ ፣ ለገጎራ ፣ ለገሂዳ ናቸው ።

ስለ አቀማመጣቸውና አስተዳደራቸው የጳጳሳቱ ድልድል ሲያብራራ "መንፈቁን ወረይሉ ፣ መንፈቁን ደሴ እየተቀመጡ ያስተምሩ ። ሲዛወሩም በበታችዎ ሊቀ ካህናት ሆኖ ሕግ የሚጠብቅልዎ የተደባበ ማርያምና የሐይቅ መምህር ይሁንልዎ ። እድራሻዎም ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተሳዊ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ ይባል" ይላል ። ደመወዛቸውም በወር 500 ብር ነበር ።

1ኛ ዓመት ቁጥር 8.9.10 ከሰኔ 30 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1938 ዓ.ም. የወጣው ዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ስለ አቡነ ጴጥሮስ ትውልድ ሲያትት "...... በ1885 ዓ.ም. ፍቼ ከተማ ተወለዱ ። ስማቸው ኃይለማርያም ነበር ።........"ይላል ። ከዚሁ ዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ላይ እንደተገኘው አቶ ኃይለማርያም በ1909 ዓ.ም መነኰሱ ። በ1910 ዓ.ም. በወላሞ ወረዳ የደብረ መንክራት ገዳም መምህር ተብለው ተሾሙ ። በ1916 ዓ.ም. በዝዋይ ደሴት የገዳሙ መምህር ሆኑ ። በ1921 ዓ.ም በእስክንድርያ ቅዱስ ማርቆስ ከአራት ጳጳሳት ጋር ጳጳስ ሲሆኑ ስማቸውም ጴጥሮስ ተባለ ።

የኢጣሊያ ፋሺስት ጦር በኢትዮጵያ ላይ በተነሳ ጊዜ በሰሜን ጦር ግንባር ዘምተዋል ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል ሆኖ ከተመለሰ በኋላ አቡነ ጴጥሮስ ሚያዝያ 24 ቀን ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገቡ ። ከዚያም ሆነው የሰላሌን አርበኞች በስብከት ያነቃቁ ጀመር ። በዚህም ለኢጣሊያ የገቡና በኢጣሊያ አገዛዝ ያመኑ የኢትዮጵያ ቀሳውስት አቡነ ጴጥሮስ ለኢጣሊያ እንዲገቡና በኢጣሊያ ላይ የሚነዙትን አጉል ስብከት እንዲተዉ በደብዳቤም በቃልም ይመክሩዋቸው ጀመር ። አቡነ ጴጥሮስ ግን ማንኛውንም ልመና አልተቀበሉትም ።

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ በኢጣሊያ ወታደሮች ከተያዘች ጀምሮ ሰላም አልነበረችም ። አርበኞች አንድ ቀን ከተማይቱን ይይዟታል እየተባለም ይፈራ ነበር ። በተለይ የመጀመሪያው ወር ለኢጣሊያኖች የጭንቅ ወር ነበር ። ማርያ ጃኮኒያ ላንድ ፣ በመጽሐፍዋ ውስጥ ሐምሌ 18 ቀን የያዘኩት ማስታወሻ ብላ ስትገልጽ "......በየቀኑ ከተማዋ እንደምትጠቃ ይነገራል ። እንደሚወራው የክረምት ወራት እስኪያልቅ ድረስ ሰላም የለም ይላሉ ። አበሾች ባልታሰበና ባልታወቀ ቀን ገበያውን ሁሉ እንደሚወሩት ይነገራል ።......" ብላለች ። እንደተፈራውም አልቀረ ተወረረ ።

ላ ኮንኩይታ ዴል ኢምፔሮ በሚል ርእስ ዞሊ (Zoli) ባሳተመው መጽሐፉ "..........በሰሜናዊ ምዕራብ በኩል እና በደቡባዊ ምሥራቅ በኩል አዲስ አበባ ከተማ ሐምሌ 28 ቀን በሁለት አቅጣጫ በኢትዮጲያውያን ተወረረች ።" ብሏል ። በእንግሊዝ ለጋሲዮን የነበረው ፓትሪክ ሮበርትስ ለእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሐምሌ 30 ቀን እ.ኤ.አ. ባስተላለፈው ሪፖርት "......የኢትዮጵያውያን ኃይል



በምዕራብ በኩል አጠቃ ። ኢትዮጵያውያኖች የሚያስገርምና ከባድ ወጊያም አደረጉ ።....... ወደ አዲስ አበባ ከተማ እየተጠጉ ሲሄዱም ጥቅጥቅ ካለው ደን ውስጥ ሲገቡ የኢጣሊያ ተከላካይ ወታደሮች ጉዳት አደረሱባቸው ። ሁለት ቀን ሙሉ በጀግንነት ተዋግተው ኢትዮጵያውያኖቹ ይዘውት የነበረውን ቦታ ትተው ሲመለሱ ጳጳሱ አቡነ ጴጥሮስ ተማረኩ ። አቡነ ጴጥሮስ ከተማዋ ድረስ ከአርበኞቹ ጋር አብረው የመጡ ናቸው ። የተያዙትም በጦርነቱ ውስጥ ነው ........"ብሏል ።

ፓጃሊ የተባለ በዚያ ዘመን የኮሪየር ዴላ ሴራ ጋዜጠኛ የነበረው ድአሪዮ ኢ.ኦ.ኢ. በሚል ርእስ ባሳተመው መጽሐፉ "....ሐምሌ 30 ቀን (እ.ኤ.አ.) በጳጳሱ ላይ የተቋቋመው ችሎት ፣ ሕዝብ በተሰበሰበበት በአደባባይ እንዲገደሉ ፈረደ ። ይህ ሲሰማ በከተማው ሕዝብ ዘንድ ሽብር ፈጠረ ። ጉዳዩም በጋዜጣ እንዳይወጣ ፋሺስቶች ታላቅ ቁጥጥር አደረጉ ። ለኛም ትዕዛዝ ተሰጠን ። ማንኛውም ጋዜጠኛ አቡኑ ተገደሉ ብሎ ወደ ኢጣሊያ አገር ቴሌግራም እንዳያደርግ ክልክል ነው ። አቡኑ ታሰሩ ብላችሁ ግን ዜናውን ማስተላለፍ ትችላላችሁ አሉን ።

"........አቡኑ ሲገደሉ በዚያው ነበርኩ ። ጴጥሮስ ረጅምና ብሩህ ገጽታ ያላቸው ናቸው ። ጥቁር ካባ ለብሰዋል ። በጉዞው ምክንያት ልብሳቸው ሁሉ በጭቃ ተበላሽቷል ።......የሆቴል ቤቱ ጌታ ግሪካዊው ማንድራኮስ የአቡኑን ንግግር ለጋዜጠኞች ያስተረጉም ነበር ። አቡኑ በሚገባ የመከላከያ አሳባቸውን ሰጡ ።

"......የሞት ፍርዱ በተፈረደባቸው ጊዜ በፀጥታ አዳመጡ ። በቀኝ እጃቸው በሰማያዊ ጨርቅ የተሸፈነ መስቀል ይዘዋል ።...... የሞት ፍርዱ ከተፈረደ በኋላ ኢጣሊያኖቹ የመግደያውን ቦታ ለማዘጋጀት ወደ ገበያ ሄዱ ። የመግደያው ቦታ ተዘጋጅቶ ጴጥሮስ ተወሰዱ ። ፊታቸውንም ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ አድርገው ቆሙ ። በሕዝቡና በጴጥሮስ መሐል ያገር ተወላጅ ወታደሮች ቆመው ሕዝቡ እንዳይጠጋ ይከላከላሉ ።

«... ጴጥሮስ ሰዓታቸውን አውጥተው አዩ ። ወዲያውም አጠገባቸው ያለውን ኢጣሊያ ለመቀመጥ እንዲፈቅድላቸው ጠየቁት ። ቆና ብለው ሰገነት ላይ ወደ ተቀመጥነው ጋዜጠኞችና መኳንንት አይተው የመቀመጥ ጥያቄያቸውን ትተው ቀጥ ብለው ቆሙ ። ከፊታቸው ለቆሙት ጉዳዮቻቸው ተመቻቹላቸው ።.... አቡኑ ረጋ ብለው ተራመዱ ። ካራሚኒዬሮቹም ከመግደያው ቦታ እስኪቆሙላቸው ጠበቁ ። ከቦታው ሲደርሱ አንድ አስተርጓሚ ተጠግቶ 'አይንዎ እንዲሸፈን ይፈልጋሉን?' አላቸው ። እሳቸውም ሲመልሱ 'የእናንተ ጉዳይ ነው ፣ እንደወደዳችሁና እንደፈለጋችሁ አድርጉ ። ለኔ ማንኛውም ስሜት አይሰጠኝም' አሉ ።

«ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ ፊታቸውን ወደ ግድግዳው እንዲያዞሩ ተደረገ ። እሳቸውን ቀድሞ በመግደል ክብር የሚፈልጉት ስምንት ካራሚኜሮች ከጴጥሮስ 20 እርምጃ ያህል ርቀው በርከክ አሉ ። በአስተኳሹ ትእዛዝም ተኮሱ ። ጴጥሮስ ጀርባቸው በጥይት ተበሳሳና ከመሬት ላይ ወደቁ ። ወዲያው አንድ ኢጣሊያዊ ካፒቴን ሐኪም ሬሳቸውን መረመረና ይሄ ቄስ አልሞተም ብሎ ተናገረ ። የካራሚኜሮቹ መኰንን ተጠግቶ ሶስት ጥይት ተኩሶ ራሳቸውን ደበደበና ጨረሳቸው። እስ ገዳዩ ኰሎኔልም የጴጥሮስን ሬሣ ማየት ቀፎት እንደ እብድ ሆኖ ከመቀመጫው ተነሳና «የት ነው የሚቀበረው!?» ብሎ ጮኸ ። ሬሣቸውም ከከተማ ውጭ ተወስዶ በሚስጢር ተቀበረ ....» በማለት ጽፏል ።

ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ እንደፃፈው «.....ከሚገደሉበት ሥፍራ ሲደርሱ አራቱን ማዕዘን በመስቀላቸው ባረኩ ።በሕዝቡም ፊት ቆመው እንዲህ አሉ ። ፋሽስቶች ያገራችንን አርበኞች ሽፍታ ቢሏቸው እውነት አይምሰላችሁ ። ሽፍታ ማለት ያለ ሀገሩ መጥቶ የሰውን አገር የሚወር ይህ በመካከላችሁ የቆመ አረመኔው የኢጣሊያ ፋሽስት ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሱ እንዳይገዛ ውጉዝ ነው ። የኢትዮጵያም መሬት እንዳትቀበለው የተገዘተች ትሁን ብለው ተናገሩ ።....»

# የካቲት 12 ቀን

የኔፕልስ ልዕልት በመወለዷ ግራዚያኒ የደስታ መግለጫ ገንዘብ እሰጣለሁ ብሎ ከዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከድሮው ቤተ መንግሥት ድሆች እንዲሰበሰቡ አዘዘ ። ከድሆቹም በስተቀር ታላላቅ የኢጣሊያ ሹማምንት ፣ የሜትሮፖሊታን ጳጳስ አቡነ ኪርልና ሌሎችም መኳንንት ነበሩ ። ለእያንዳንዱ ድሃም ሁለት ማርትሬዚያ ብር እንዲሰጥ ተወስኖ ነበር ።

እኩለ ቀን ገደማ ላይ 3000 የሚሆኑ ድሆች ከቤተ መንግሥቱ ገቡ ። ወዲያው በግቢው በር በኩል አንድ ቦምብ ፈነዳ ። ቀጥሎም ሌላ ፈነዳ ። ለ3ኛ ጊዜ የተጣለው ቦምብ የፋሽስት ኢጣሊያ መኳንንት ካሉበት ቦታ ፈነዳ ። ግራዚያኒ ጀርባውን ቆስሎ ወደቀ ። በቀጠለው ጥቂት ደቂቃ ውስጥ ሌሎች ቦምቦች ተከታትለው ተጣሉ ። በጠቅላላው በግቢው ውስጥ ሰባት ቦምቦች ፈነዱ ። ጄኔራል ሊታዩ ፣ የአዲስ አበባው ከንቲባ ጉይዶ ኮርቴሲ ፣ ጋዜጠኛው ማርዮ አፔሎስና ሌሎች 30 ያህል ሰዎች ቆሰሉ ። የቦምቡ ፍንዳታ ጋብ እንዳለ አድፍጠው ተኝተው የነበሩ ካራሚኜሮች ተነስተው ተኩስ ከፈቱ ። በዚያ ግቢ ውስጥ ያለማቋረጥ ስስት ሰዓት ሙሉ ተኩስ ተካሄደ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባለ ጥቁር ሸሚዞች ፣ የኢጣሊያ ሾፌሮች ፣ የቅኝ ግዛት ወታደሮች በአዲስ አበባ ከተማ እየዞሩ ሕዝቡን ይፈጁት ጀመር ።

አንጀሎ ዴል ቦካ በመጽሐፉ«.... በአዲስ አበባ የሚኖር አንድ ኢጣሊያዊ ወዳጄ ሲኞር ዲ ስሜን አትግለጥብኝ ብሎ እንዲህ ሲል አጫወተኝ ። እየሀ የዚያን ዕለት ብዙ ኢጣሊያኖች ብዙ ሥራ ሠርተዋል ። ወደማታ ገደማ ካንድ ጓደኛዬ ጋር ስንገናኝ ያ ጓደኛዬ ቦምብ ስጥል የዋልኩበት እጄ ዝሏል ብሎ ነገረኝ ። አንዱ ኢጣሊያዊ ሲያጫውተኝ ባንዲት ትንሽ ጣሳ በያዝኳት ቤንዚን አስር ቤቶች አቃጠልኩባት አለኝ ። በዋናው የጦርነት ጊዜ ጥይት ተኩሰው የማያውቁ ኢጣሊያውያኖች ሁሉ በዚያን ቀን ሲተኩሱ ዋሉ ሲል አጫወተኝ....» በማለት ጽፏል ።

አዲስ አበባ የነበረው የሀንጋሪው ሐኪም ዶክተር ላዲስላስ ሳቫ ደግሞ «..... ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሰላምና በፍቅር ከቤተ መንግሥቱ ግቢ ተሰበሰቡ ። ጥቂት ቆይቶ ግራዚያኒና መኳንንቱ ከተቀመጡበት ጠረጴዛ አጠገብ ቦምቦች ተወረወሩ። ቦምቡ እንደተጣለ ግራዚያኒ ጠረጴዛው ሥር ተደበቀ ። ሌሎቹ ኢጣሊያኖች ግን ከመሬት ተኙ ። ቦምቡን የጣለው በኢጣሊያኖቹ ዘንድ በአስተርጓሚነት የሚሠራ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ነው ።

«ለጥቂት ጊዜ ፀጥ አለ ። ኢጣሊያኖቹ ሌላ የሚወረወር ቦምብ እንደ ሌለ ካወቁ በኋላ ከተኙበት ተነሱ ። ወዲያው ኮርቴሲ ወደ ኢትዮጵያውያን መኳንንት ሽጉጡን እነጣጥሮ የመጀመሪያዋን አንድ ጥይት ተኮሰ ። ካራቢኔሪዎችም ምሳሌውን ተከተሉ ። በጥቂት ጊዜ ውስጥም በዚያ ግቢ 300 ሬሣዎች ተከመሩ ።

«ኃይለኛና ተገቢ ያልሆነ ጭፍጨፋ ነበር ። ሽማግሌዎች ፣ እውሮች ፣ እግር የሌላቸው ለማኞች ፣ ድሆች እናቶች ከነልጆቻቸው ነበሩበት ። ባለጥቁር ሸሚዞች በግቢው እየተሯሯጡ በሕይወት ያለ ኢትዮጵያዊ ይፈልጉ ነበር ። ከሬሣዎቹ መሀልም የሚተነፍስ እንዳለ እያሉ እየመረመሩ ይገድሉ ነበር ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ባለጥቁር ሸሚዞች ፣ ካራቢኔሪዎችና የጦር ወታደሮች በከተማው ውስጥ ይሯሯጡ ጀመር ። ሱቆቹ ሁሉ እንዲዘጉ አደረጉ ። የውጭ አገር ሰዎችም ከቤታቸው እንዳይወጡ አዘዙ ። በተለይ ፎቶግራፍ ማንሻ እየተፈተሸ ይወሰድ ጀመር ።መንገዱ ሁሉ ጭር አለ ። የፖስታና የስልክ አገልግሎት ተቋረጠ ። በቤተ መንግሥቱና በአካባቢው ያሉት መንገዶች በሙሉ በሬሣ ተሸፈኑ ።

«ምን ዓይነት እጨካከን ነው ? ደም እንደ ውሃ ሲፈስ በየመንገዱ ላይ ያየሁት የዚያን ጊዜ ነው ። የወንዶች ፣ የሴቶች ፣ የልጆች ሬሣ በያለበት ተኝቷል ። ወዲያ ውም ከባድ የቃጠሎ ጭስ ተነስቶ ከተማዋን አጨለማት ። የሕዝቡ ቤት ከተፈ ተሸ በኋላ ሰዎቹ በውስጡ እንዳሉ ቤቱ በእሳት ይቃጠላል ። ቃጠሎው ቶሎ እንዲ ያያዝም በቤንዚንና በዘይት ይጠቀሙ ነበር ። ሰዉ እሳቱን እየሸሸ ከቤቱ ሲወጣ በመትረየስ ይገድሉታል ። ሌሊቱንም ሲገድሉና ሲያቃጥሉ አደሩ ። የማልረሳው ነገር ፣ በዚያ ሌሊት የኢጣሊያ መኰንኖች በሚያማምር አውቶሞቢላቸው ከሚስቶ ቻቸው ጋር ሆነው ብዙ ሬሣ ከተከመረበትና ብዙ ቃጠሎ ከሚታይበት ቦታ በሰው ደም ላይ እየቆሙ ያን እልቂት እየተመለከቱ ይስቁ የነበረበት ሁኔታ ነው።

«ግራዚያኒን ሆስፒታል አስገብተውታል ። ግራዚያኒ ሆስፒታል ውስጥ ሆኖ በመስኮት የከተማዋን መቃጠል እያየ ይስቅ ነበር ። ዳግማዊ ኔሮ ። በዓለም ጦርነት ጊዜ ቁስለኛ ለማንሳት ከግንባር ቀደሙ ጦር ጋር በአንቡላንስ ውስጥ እሠራ ነበር። በሌላም ጦርነቶች ተካፋይ ሆኛለሁ ። እንደ አዲስ አበባው ያለ እልቂት ግን አላ የሁም ።

«መኪናዎች እየዞሩ ሬሣ ያነሳሉ ። ባለጥቁር ሸሚዞች ወደ ኢጣሊያ ባንክ እየገቡ ሌሊት የሰረቁትን ብርና ወርቅ ያስቀምጣሉ ። ዘረፋው በቤት ውስጥ ብቻ አልነበረም ። ከሚገድሏቸው ሴቶች አንገትና ጆሮ ላይ የሚገኘውን ወርቅ ሁሉ ይወስዱ ነበር ።

«ሕክምና በምሠራበት ቦታ ብዙ ኢጣሊያኖች ይመጡ ነበር ። እያንዳንዱ ኢጣሊያም ምን ያህል ሰው እንደገደለ በኩራት ይናገራል ። አንዳንዶቹ 80 ገደልኩ ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ መቶ እንደገደሉ ይናገራሉ ። አንድ ኢጣሊያዊ ብቻ እያ ዘን እኔስ የገደልኩት ሁለት ብቻ ነው ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ ። ....የማልረሳው ነገር ፣ ግድያው እንዲቆም በተደረገበት ጊዜ ታላቁ ግራዚያኒ ለሕዝብ በማዘን ግድ ያው ይቁም ብለዋል ተብሎ የተነገረው ነው ። ግሩም አዘኔታ ፣ ....» በማለት በሰፊው ጽፏል ።

በቁጥር 14154 ግራዚያኒ ሮማ ላለው ለቅኝ ግዛት ሚኒስትር ባስተላለፈው ቴሌግራም «እነኚህ ጥቁሮች የኛን ወታደር ሲያዩ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ይላሉ። ይህን የሚሉትንም ለመቀጣጫ ሁሉንም አስጨረስኳቸው ። እደግመዋለሁ ፣ አስጨ ረስኳቸው» ብሏል ። በዚያው ዘመን እ.ኤ.አ. የካቲት 22 ቀን (በኛ የካቲት 14) የወጣው ጋዜጣ ዴል ፖፖሎ ሲጽፍ«.....የአዲስ አበባ አጋማሽ በእሳው ጸድ ቷል ። 2000 ኢትዮጵያውያን ተይዘው ወደ ደናኔና ወደሌሎቹም ማሰሪያ ቦታዎች ተልከዋል.....» ይላል ።

የካቲት 12 ቀን በተጀመረው እልቂት በሶስት ቀን ውስጥ 30.000 ሰዎች በአ ዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከተገደሉ በኋላ ሌላው እየታፈሰ ወደ በረሃ እሥር ቤቶች ተላከ ። እስር ቤቶቹ እንዴት ነበሩ ? ለጦር ወንጀለኞች አጣሪ ኮሚቴ ፣ ብላታ በቀለ ሀብተ ሚካኤል ከተናገሩት ውስጥ በመጠኑ እንጥቀስ ። «.....መቃዲሾ እንደደረ ስን በቀጥታ ከዋናው ወህኒ ቤት አገቡን ። በማግሥቱም ወደ ደናኔ ወሰዱን ።200 ሰዎች ባንድ ቦታ አጐሩን ። ይሰጡን የነበረው ምግብ ለጤናችን ፈጽሞ የማይ ስማማን ነበር ።

«የሚሰጡንም በላዩ ላይ ብዙ ትላትሎች የሚታዩበት የደረቀ ቂጣና ሻይ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙዎቻችን ታመምን ። የዚያን ጊዜ የእስር ቤቱ ኃላፊ ብርጋ ዲየር ባሮኒ ነበር ። ስለምግባችን ብዙ ጊዜ እየቀረብን ብናመለክትም ትእዛዙ የበ ላይ ስለሆነ ምንም ማድረግ እንደማይቻል ይነግረን ነበር ። በግራዚያኒ ሕይወት ላይ አደጋ ከተጣለ በኋላ ብዙ እስረኞች ወደኛ መጡ ። ቦታ ስለጠበበ ሜዳው በሽቦ ድጥሮ ከዚያ ሰፈሩ ። እኛንም ወስደው ከነሱ ጋር ደባለቁን ። ከተደባለቅን

በኋላ የምግብ ጉዳይ የባሰ ሆነ ። በምግቡ ምክንያት በየቀኑ አራትና አምስት ሰዎች እየሞቱ ይጣሉ ጀመር.....» ብለዋል ። የተባበሩት መንግሥታት ከተመሠረት በኋላ በዚሁ ስር ለተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ቃላቸውን ከሰጡት እስረኞች መሀል ሌላው አቶ ሚካኤል ተሰማ ናቸው ። እሳቸውም እንዲህ ብለው ነበር ።«....በደናኔ እስር ቦታ 3 ዓመት ከ3 ወር ታስሬ ቆይቻለሁ ። የወህኒ ቤቱም ሁኔታ እንዲህ ነበር ። ላንድ ወታደር ማደሪያ የተሠራች አንዲት ድንኳን ለሶስት ኢትዮጵያውያን ተሰጠችን ።ምግባችን የደረቀ ጋሌታ ነው ። የውቅያኖሱን ውሃ መጠጣት እንደጀመርንም ብዙዎቻችን ታመምን ። በየቀኑ ከስድስት እስከ 30 ሰዎች በተቅማጥ በሽታ ይሞቱ ነበር ። በጠቅላላውም 3175 ሰዎች ሞቱ ። ይህንንም ቁጥር ለማወቅ የቻልኩት በክሊኒኩ ውስጥ ረዳት ሐኪምና የበሽተኞች ሁኔታ መዝጋቢ ስለነበርኩ ነው ። በደናኔ እስር ቤት የነበርነው 6,500 ሰዎች ነን ። ከነዚሁ ውስጥ 3175 ሰዎች ሞቱ ። ዓመት ከታሠርን በኋላ ሥጋ ፣ ማካሮኒና ሩዝ በሣምንት አንድ ጊዜ ይሰጠን ጀመር ። እስረኞቹን ይጠብቁ ከነበሩ ኢጣሊያኖች መሀል ብርጋዲየር ባሮኒ ፣ 50 አለቃ ቶሳቶ እና አሁን ስሙን የረሳሁት የካራሚኔሪዎች ማርሻል እስረኞችን በመግረፍ የታወቁ ነበሩ ።

“ሥራችን አትክልት መኮትኮት ፣ የሚነድ እንጨት መስበርና መንገድ መሥራት ነበር ። በሥራ ቦታ ድካም የሚያሳዩ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች እጆቻቸውን የኋሊት እየታሠሩ ለሰባት ቀናት ጣርያ ላይ ይንጠለጠላሉ ። በእንዲህ ያለው ቅጣትም ሁለት ሰዎች እጆቻቸው እየተገነጠሉ ሞተዋል ። እስረኛ ታሞ ወደ ክሊኒክ በሚመጣበት ጊዜ ካፒቴን አንቶኒዮ እነዚህ ሰዎች ከሚኖሩ ቢሞቱ ይሻላቸዋል በማለት አርሴኒክና እስትሪቺኒን የተባሉ መርዞችን በመርፌ በመውጋት ይገድላቸው ነበር ። አንዳንዶቹንም ለሕክምና የሚመጡትን እጅና እግራቸውን እያሰሩ ገላቸውን በምላጭ በመተልተል ይጫወቱባቸው ነበር ።......” ሲሉ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል።

የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ደጃዝማች ሪሳሪዮ ጊላ እግዚእ በግራዚያኒ ላይ ቦምብ በተጣለ ጊዜ ከዚያው ስለነበሩ የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ። ደጃዝማች በእውነት እመሰክራለሁ ብለው ከማሉ በኋላ “........የተኩስ ድምፅ ሰማሁ ። መኪናዎች እዚህም እዚያም ይሯሯጣሉ ። ሰውም ይሯሯጣል ። መትረየስ ይተኮሳል ። ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሏል ። ኢትዮጵያውያኖች ከኢጣሊያኖች ይሸሻሉ ። ኢጣሊያኖቹ ደግሞ ከኢትዮጵያውያኖቹ ይሸሻሉ ። ኢጣሊያኖቹ እንደገመቱት በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ከብቦ የነበረው ሽፍታ ከተማዋን የወረራት መሰላቸዋል ። ከዚያ በፊት ራስ ደስታ ከአዲስ አበባ ገብተው የኢትዮጵያ አርበኞች ከከተማዋ ያለውን ኢጣሊያዊ በሙሉ ይገድላሉ እየተባለ ይወራ ስለነበር ነው.....” ብለዋል ።

ደጃዝማች ሪሳሪዮ ከሁለት ኢጣሊያኖች ጋር ወደፋሺስት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ሄደው በዚያ ስላዩት ሲናገሩ “.......ከፋሺስት ዋና ፀሐፊ ከጉይዶ ኮርቴሲ ጋር ተገናኘን ። ዙሪያውንም ብዙ የፋሺስት ሹማምንት አሉ ። ኮርቴሲም ለነኛ የፋሺስት መኰንኖች..... ወንድሞቼ ሆይ ፣ ዛሬ ድል የማድረጋችንና የበላይነታችንን የማሳወቂያ ቀናችን ነው ። በዚች በሶስት ቀን ውስጥ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ አጥፉ ። ለዚህ ለሶስት ቀን የሚሆንም የነጭ ሽብር (ካርታ ቢያንካ) ፈቃድ እሰጣችኋለሁ ። ይህም ፈቃድ ለማጥፋት ፣ ለመግደልና በኢትዮጵያውያኖች ላይ የፈለጋችሁትን ለማድረግ የሚያስችላችሁ ነው አላቸው ።

“ከዚህ በኋላ እነኚያ የፋሺስት መኰንኖች ወጥተው ሄዱ ። ሁሉም የጦር መሣሪያቸውን በክንዳቸው እንደያዙ ነበር ። ልክ እንደወጡም ሥራቸውን ጀመሩ ። በካራሚኔሪዎች ያልታሠረ ፣ በመንገድ ላይ ሲሄድ ወይም እቤቱ ውስጥ አርፎ የተቀመጠው ሁሉ ተገደለ ።......ቤቶች ሲቃጠሉ አይቻለሁ ።......ከሚቃጠለው ቤት ልጆች ሲወጡ በኢጣሊያኖቹ እየተገፉ ከእሳቱ ውስጥ ሲጨመሩ አይቻለሁ ።

“በማግሥቱ ቅዳሜ ቀን ነበር ። በዚያም ቀን ኢጣሊያኖች ትንንሽ ቤቶችን ሲያቃጥሉ ዋሉ ። በትልልቆቹ ቤቶች ላይ ግን ስማቸውን እየፃፉባቸው ያልፉሉ ። ይህም ቤቱ የተያዘ መሆኑን ለመግለጽ ያህል ነው ።.....” በማለት መስክረዋል ።

ፎር ጉድ ኤንድ ኤምፐረር በተባለው ድርሰታቸው ሚሲዮናውያኖቹ ኸር በርት እና ዴላ ሀንሰን እንደፃፉት "....አዲስ አበባ የደረስነው እልቂቱ ከቆመ በኋላ ነው ። ከዚህ በፊት የሕዝቡ መኖሪያ የነበሩ ቤቶች በሙሉ ተቃጥለዋል ። ሌላው ቀርቶ የሆስፒታል ግድግዳዎች እንኳ በእሳት ተለብልበው ይታያሉ ። በከተማዋ በሙሉ የሚታየው የከሰለ ቤት ፍራሽና በእሳት ተለብልቦ የጠቆረ ግንብ ነው ። ይህንንም በማየታችን ልባችን በሀዘን ተነካ ። በተለይም በጣም ያሳዘነን ነገር ፣ ቤቶች ሁሉ የተቃጠሉት ፣ ነዋሪዎች ከውስጣቸው እንዳሉ ነው ካሉን በኋላ ነው ።..." ብለዋል ። በዚያን ቀን ስለተካሄደው እልቂት ብዙ የዓይን ምስክሮች ብዙ አሰቃቂ ድርጊቶችን መስክረዋል ። የሁሉንም ለማጠቃለል ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚወጣው ስለ ሆነ ትቼዋለሁ ።

ጋዜጠኛው ቺሮ ፖጃሊ የካቲት 13 ቀን ስላየው ሁኔታ "......ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች መደበቃቸው ስለተሰማ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ቤንዚን ተረጭቶ እሳት ተለቀቀበት ። ይህንንም ያዘዘው ኮርቴሲ ነው ።.... የቤተ ክርስቲያኑ መጻሕፍትና ስዕሎች ተቃጠሉ ።....ከቤተክርስቲያኑ ውስጥ ከእሳቱ ለመሸሽ 50 ያህል ሰዎች ሲወጡ ተያዙና ከቤተ ክርስቲያኑ ጓሮ ተወስደው በእሳት ይቃጠሉ ሲባል አንድ ኰሎኔል አዝኖላቸው መቃጠሉ ቀርቶ በቦምብ ይገደሉ ብሎ አዘዘና በሙሉ ተገደሉ ።...በዚህ ቀን ኰሎኔል ማዚ (Mazzi) የጠቅላላው የመገናኛ ራዲዮ ኃላፊ እንዳጫወተኝ ሶስት ጀኔራሎች መሞታቸው ተላልፏል አለኝ ........"በማለት በመጽሐፉ ጽፎታል ።

የካቲት 12 ቀን ስለደረሰበት አደጋ ግራዚያኒ ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ቴሌግራም ልኮ ነበር ። የዚያም ቴሌግራም ግልባጭ በኢትዮጵያ ላሉ የኢጣልያ ሹማምንት ተላልፎ ነበር ። ግራዚያኒ ባስተላለፈው ቴሌግራም "......ዛሬ ጧት በ11 ሰዓት (በኛ 5 ሰዓት) ግቢ ተገኝቼ ነበር ። ታላላቅ መኳንንት ፣ የኦርቶዶክስና የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች ሁሉ ተሰብስበው ነበር ። የስብሰባው ዋና ምክንያት የኔፕልስ መስፍን ስለተወለደ ሶስት ሺ ለሚሆኑ ድሆች ምፅዋት ለመስጠት ነበር ። 12 ሰዓት ሲሆን (በኛ 6 ሰዓት) በተሰበሰበው መኳንንት መሐል አሥር የብሬዳ ሥራ (Breda) የጅ ቦምቦች ካልታወቁ ሰዎች ተጣሉብን ። በዚህም ምክንያት ሰላሳ ሰዎች ቆሰሉ ። .....በኔ መቁሰል ምክንያት አገሪቱን የተከበሩ ፔትሬቴ እና ጀኔራል ጋሪባልዲ በሕብረት እንዲጠብቁ አድርጌአለሁ ። ለአዲስ አበባ ከተማ ፀጥታም አላፊ አድርጌአቸዋለሁ ።..."ብሏል ።


በሌላ ቀን ባስተላለፈው ቴሌግራሙ ደግሞ "......የተጣለብኝ ቦምብ ቢያንስ 18 ይሆናል ። አሳባቸው ባንድ ፈንጂ እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የመንግሥቱን ባለሥልጣኖች ጠራርጎ ለማጥፋት ነበር ። .......ሊሆን ግን አልቻለም ። ......የአዲስ አበባ ሰዎችም ጉዳይ ታውቋል ። የአዲስ አበባን ከተማ ዙሪያ ከከበበው ሽፍታ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው የመከላከያ ኃይላችንን ከጀርባው ይወጉታል ።.....በተጣለብኝም ቦምብ 250 ፍንጥርጣሪ ብረቶች ከገላዬ ወጥተዋል ። እነኚህንም ፍንጥርጣሪዎች ለታላቅ መታሰቢያነት አስቀምጫቸዋለሁ ።......"ብሏል ።

ግራዚያኒ የየካቲት 12 ቀንን እልቂት ባዘዘ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የነበረው የኢጣሊያ ወታደር 35,000 ሜትሮፖሊታን ወታደሮች ፣ 40,000ባለ ጥቁር ሸሚዝ ሚሊሺያ ፣ 5,000 የኤርትራ ፣ 3,000 የሊቢያ ተወላጅ ወታደሮች ነበሩ ። የኤርትራ ተወላጅ ወታደሮች "እኛ ወታደሮች ነን ። ከተማ ውስጥ ከቤትና መኖሪያ ከሌላው ጋር በጥይት ተኩስ አንተኩስም" በማለታቸው ብዙዎቹ ጦር ሠፈራቸው ውስጥ ተገደሉ ። ሌሎችም ታሰሩ ።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ዛሬ ዩኒቨርሲቲ በሆነው ግቢ ውስጥ ቦምቦች ሲፈነዱ ቦምቦቹ የተጣሉት ከሁለት ይሁን ከብዙ ሰዎች እስካሁን የታወቀ መረጃ የለም ። ግራዚያኒ እጠገብ የፈነዳውን ግን አብርሃ ደቦጭ ከጓደኛው ከሞገስ አስገዶም ጋር እንደጣለው ይነገራል ።




ለዚች ሕፃን መወለድ የደስታ ስጦታ ለመስጠት ነበር ሕዝብ የተጠራው።




ሕዝቡ እንዲሰበሰብ የተጠራበት የድሮው ቤተ መንግሥት ።



ሕዝቡ እንዲረጋ ታዘዘ ።




"አትጋቶ !"




ከአደጋው በኋላ ሕዝቡ እየታፈሰ ከድሮው ማዘጋጃ ቤት ሲገባ ።



ፋሽስቶች ፣ እየተሰበሰበ የሚታሠረውን ሕዝብ በአጠና እየደበደቡ ሲቀበሉ ።




ሕዝቡ በተርታ ሆኖ እስር ቤት ይገባ ጀመር ።



የወገኖች አወዳደቅ ።



የአዲስ አበባ መንገዶች በሬሣ ተሞሉ ።



ከተማዋ ፈራረሰች ። ሕዝቡም ታፈሰ ።




ሬሳዎች ይቆለሉ ጀመር።




ሬሳዎች ሲራገፉ።




ጉድጓድ ቆፋሪዎች ታላላቅ ጉድጓዶችን ቆፈሩ ።



ሬሣዎች በመኪና እየሞሉ ከከተማ ውጭ ተጓ




ሬሣዎች በመኪና እየተጓዙ ከዱር ተጣሉ ።




ሬሳዎች ዱር ውስጥ ከመኪና ይራገፉ ጀመር ።



ሬሳዎችን ለማቃጠል ቤንዚን በበርሜል ቀረበ ።



በጕድጓድ የተሞላ ሬሣ ።



ፋሺስት ከለቀቀ በኋላ አጽሞች እየተቆፈሩ ወጡ ።



የካቲት 12 ቀን በግፍ ለተገደሉ ኢትዮጵያውያን በአዲስ አበባ የቆመው ሐውልት ።



አብርሃ ደቦጭ ።



አብርሃ ደቦጭ ።

# አብርሃ ደቦጭ

አብርሃ ደቦጭ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ነው። የፋሺስት ወረራ በኢትዮጵያ ላይ በተነሳበት ጊዜ አብርሃ ደቦጭ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ይማር ነበር። አብርሃ ደቦጭ ኢጣሊያንኛ ተምሮ ስለነበር አዲስ አበባ ውስጥ ኢጣሊያ ሌጋሲዮን የሚሠሩትን ዘመዶቹን ለመጠየቅ እየሄደ በዚያ ካሉ ኢጣ ሊያኖች ጋር ተዋውቋል ። ወደ ኢጣሊያ ሌጋሲዮን መመላለሱና ከኢጣሊያ ኖች ጋር መተዋወቁም አጠራጥሮት አብርሃ ደቦጭ ተይዞ ታሰረ። የታሰረው እፈ ንጉሥ ከልካይ ቤት ውስጥ ነበር። ኢጣሊያ አዲስ አበባን በያዘ ጊዜ አብርሃ ደቦጭ ተፈታ። ከዚያም በኋላ የግራዝማች አበራ ግዛውን ዘመድ በሚስትነት አግብቶ መኖር ጀመረ።

አብርሃ ደቦጭ ኢጣሊያንኛ ተምሮ ስለነበር አዲስ አበባ ባለው በፋሺስት ፖለቲካ ቢሮ ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ጀመር። ከሞገስ አስገዶም ጋር ጓደኛ ሆነዋል። ሞገስ አስገዶም የሚኖረው ስብሃት ከሚባል ጓደኛው ጋር ነው። ስብሃት ደግሞ የሚሠራው ከጀርመን ኮንስላር ሚሲዮን ውስጥ ነው።

አብርሃ ደቦጭ የኢጣሊያኖችን የግፍ አሠራርና ትእዛዝ እያየ ለጓደኞቹ ያጫውት ጀመር። እንዲህ ዓይነቱን ጨዋታ ብዙ ጊዜ የሚጫወቱት ስብሃት ከሚሠራበት ከጀርመን ኮንስላር ሚሽን ውስጥ ነው። ጀርመን፣ የኢጣሊያ መንግሥት ደጋፊና ወዳጅ ስለነበር በነአብርሃ ደቦጭ መሰብሰብ ጠርጣሪ የለም ነበር።

ይህም ብቻ ሳይሆን አብርሃ በኢጣሊያ ፖሊቲካ ቢሮ ውስጥ የሚሠራ ሰው ስለነበር ከውጭ ያለው ሰው በክፉ ዓይን እያየው ስለሚጠላው የሚያጫውተው ቀርቶ የሚያስጠጋውም አልነበረም።

ይህን የመሳሰለው ነገር ሁሉ አብርሃን ያስቆጨዋል። ኢጣሊያኖችን ለመበቀልም ቆረጠ። ጫማ አውልቆ በባዶ እግሩ መሄድ ጀመረ። ጫማ ማድረግ የተወበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት። 1ኛው እግሩን ለማጠንከር ሲሆን፣ 2ኛው ደግሞ ያን የተቀደደበትን ጫማ መለወጫ በማጣቱ ነበር። ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮፒያ ኒውስ ይባል በነበረው ጋዜጣ ላይ አልአዛር ተስፋ ሚካኤል እንደጻፈለት "አብርሃ ደቦጭ ጫማ በሌለው እግሩ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ 10 እና 15 ኪሎ ሜትር እየራቀ መሄድ ጀመረ። በሄደበትም ጫካ ውስጥ ድንጋይ እየወረወረ ስለ ቦምብ አጣጣል ማጥናትና ክንዱን ማጠንከር ጀመረ።" ብሎለታል።

አብርሃ ደቦጭ ጥናቱን ጨርሶ በራሱ መተማመን ሲጀምር የቤት ዕቃዎቹን በሙሉ ሸጠ። ሚስቱንም ደብረ ሊባኖስ ወስዶ አስቀመጠ።

የኢጣሊያ ልዑል፣ ልጅ ስለወለደ በአዲስ አበባ በቤተ መንግሥቱ ለልጁ መወለድ ምክንያት የደስታ ስጦታ ለማድረግ መወሰኑን ሰማ። በዚያም ቦታ በግራዚያኒና በተከታዮቹ ላይ ቦምብ ለመጣል ወሰነ። ይህንኑ ውሳኔውንም ለሚያውቃቸው ኢትዮጵያውያን ነገረ። ለበጅሮንድ ለጥ ይበሉ ገብሬ፣ ለብላታ ዳዲ፣ ለቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ፣ ለደጃዝማች ወልደ አማኑኤልና ለሌሎቹም ጉዳዩን ነግሮ ጥሪው ከተደረገበት ቦታ እንዳይወጡ አስጠነቀቃቸው። እነኚያ ከአብርሃ ደቦጭ ማስጠንቀቂያ የተነገራቸው ሰዎች አብርሃ ደቦጭን እንደሰላይ ቆጥረው «ዞር በል ወዲያ» አሉት እንጂ ሃሳቡን አልተቀበሉትም።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓም አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በዓሉ ከሚደረግበት ቦታ ቀደም ብለው ደረሱ። ከበዓሉ ቦታ ከመሄዳቸው በፊት አብርሃ ደቦጭ ቤት ውስጥ ሳንቃው ወለል ላይ የኢጣሊያን ባንዲራ አንጥፈው ዙርያውን በሚስማር መትተው በሩን ቆልፈው ነበር የወጡት ።



ሞገስ አስገዶም ።

ሁለቱም በኪሶቻቸው ቦምብ ይዘዋል ። ማረሻል ግራዚያኒ ለተሰበሰበው የአዲስ አበባ ሕዝብ ንግግር ሲያደርግ የያዙትን ቦምብ ወረወሩበት ። አምልጠውም ከግቢው ውስጥ ወጡ ። አምልጠው ከወጡ በኋላ ከአርበኛው ከራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሄደው ተደባለቁ ። ለራስ አበበም ምን አድርገው እንደወጡ አጫወቷቸው ። ጥቂት ጊዜ ከራስ አበበ ዘንድ ቆይተው ወደ ሱዳን ለመሻገር መፈለጋቸውን ነግረው አስፈቀዱ ። የሱዳን ጉዞአቸውን ጀምረው ሱዳን ሊገቡ ሲሉ ባልታወቁ ሰዎች ተገደሉ ።

—O—

# የባቡር አደጋ

በአምስቱ የጠላት ዘመን በየቦታው የተደረጉት ግጭቶች በመጠንም ቢሆን ሲወሩ የኢጣሊያን መንግሥት ወጥሮ የያዘው የባቡር ሐዲድ አደጋ ግን ስላልተወራ በአገራችን እምብዛም የታወቀ አይደለም ። የሸዋ አርበኞች ከአዲስ አበባ ጂቡቲ በሚደርሰው የባቡር ሐዲድ ላይ አደጋ መጣል የጀመሩት በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም. ነው ።

ኤል.ላ.አኖ.ዴል. ኢምፔሮ የተባለው የኢጣሊያኖች የእስታስቲክስ መጽሐፍ እንደሚገልጸው እ.ኤ.አ. ሐምሌ 6 ቀን 1936 ዓ. ም. (በኛ ሰኔ 29 ቀን 28 ዓ.ም) በባቡር ኮሚሳር ትእዛዝ ከአዲስ አበባ በ6 ሰዓት የተነሳው ባቡር 444 ኪሎ ሜትር ላይ ማለት በአቃቂና በሞጆ መሀል ሲደርስ አርበኞቹ መቱት ። ሐዲዱንም ሰባበሩ ። የመገናኛውንም ስልክ ቆራረጡ ።

የኢጣሊያ መንግሥት የባቡሩን ድርጅት ለማሻሻል በማለት አዲስ ባቡር አስመጥቶ ነበር ። ይህ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት በተነሳበት ጊዜ የመንገድ ላይ አደጋውን በመፍራት አንድ የባቡር መሀንዲሶች ቡድን ፣ አንድ ሙሉ ትጥቅ ያለው የሚሊቴሪ ፖሊሶች ቡድን ፣ አንድ የቴሌግራፊስት ሲቪል ሠራተኞችን በመያዝ ታጅቦ ነበር ። ቢሾፍቱ ከተማ አጠገብ ሲደርስ አርበኞቹ አደጋ ጣሉበት ። ይህ ነገር አዲስ አበባ ባሉ ኢጣሊያኖች ዘንድ እንደተሰማ ወዲያውኑ አካባቢውን እንዲመታ የጋሊቢያቲ ጦር ታዘዘ ።

በጋሊቢያቲ የሚመራው ጦር አደጋው በደረሰ ዕለት ሰኔ 29 ቀን 28 ዓ.ም እድአ ድርሶ ሰላማዊው ሰው የሠፈረበትን ቦታ ሁሉ ደበደበ ። ጋሊቢያቲ የባቡር ሐዲዱን አካባቢ ይደብድብ እንጂ የሐዲዱ መስመር ግንኙነቱ ተዘግቶ ነበር ። የጋሊቢያቲ ጦር የአድአን አካባቢ በሚደበድብበት ጊዜ ከጂቡቲ በባቡር ተሳፍሮ ሰኔ 30 ቀን ሞጆ የደረሰው የኮሪየሬ ዴል ሴራ ጋዜጠኛ ቺሮ ፖጃሊ (Ciro Poggiali) ስለዕለቱ ሁኔታ በመጽሐፉ ሲያብራራ «....በ15 ሰዓት ከታወቀውና ከዋናው ከተማ 70 ኪሎ ሜትር ከሚርቀው ሞጆ ከሚባለው ጣቢያ ደረስን ። በዚያም ጣቢያ በማጀር አሌሳንድሮ ጉሪኒ የሚመራ አንድ ብርጌድ ጦር አለ ። የተሳፈርንበት ባቡር ከጣቢያው እንደቆመ መጥፎ ወሬ ሰማን ። ከኛ መድረስ አንድ ቀን በፊት ከዚያ ጣቢያ የወጣ አንድ ባቡር 30 ኪሎ ሜትር ያህል እንደ ሄደ ሽፍቶች አደጋ ጥለው ባቡሩን ለሁለት ቆራረጡት አሉን ። መገናኘት እንዳይቻልም የስልኩን ሽቦ ሁሉ በጣጥሰውታል ። ወሬው ለጦር አዛዡ ለጉሪኒ የደረሰውም 20 ሰዓት ቆይቶ ነው። ....ሽፍቶቹን ፍለጋ የሄደው ጦር እስቲመለስና የመንገዱ ፀጥታ እስቲረጋገጥ ድረስ የኛ ባቡር ከዚያው ከጣቢያው እንደሚቆይ ተነገረን....በጀኔራል ጆዳ (Gioda) የሚመራ ጦርም ወደ ሥፍራው ለእሰሳ ተልኳል ።.....በባቡሩ ላይ በደረሰው አደጋ አምስት ሰዎች ሞተዋል ። ከእነኚህም አንዱ ቴኔንቴ ኰሎኔሎ (ሌ/ኰ) ማዕረግ ያለው ነው ።.....» ብሏል ።

ሐምሌ 1 ቀን 1928 ዓ.ም. ሞጆ ያለውን የኢጣሊያ ጦር ለማጠናከር ጄኔራል ጋሊና የሚመራው ጦር ታዘዘ ። ሚኤሶ እና ጉታ ላይም ተዘዋዋሪና ጠንካራ ጦር ተደረገ ። ኢል አኖ ዴል ኢምፔሮ መጽሐፍ እንደሚለው ከዚህ ቀን ጀምሮ የሐዲዱን ጥበቃ ኃላፊነት ጀኔራል ግራዚያኒ ያዘ ። ፖጃሊ ሐምሌ 1 ቀን (እ.ኤ.አ. ሉሊዩ 8 ቀን) ረቡዕ ዕለት በጻፈው ማስታወሻ «.....ለሊቱን ባቡር ላይ ተኝተን (ሞጆ) አደርን ። ሞጆ ከተማ ለሊት በሽፍቶቹ ይጠቃል ተብሎ ስለተፈራ በዚያ

ያለውን የማጀር ጉሬኒን ጦር ለማጠናከር በጀኔራል ብራሊያ (Braglia)እና በጀኔራል ጀዳ የሚመራ ጦር ሞጆ ሠፈረ ።.....በትናንትናው እለትም ከአዲስ አበባ አይሮፕላኖች ተነሥተው ሽፍቶቹ ያሉበትን ቀበሌ ሲደበድቡ ውለዋል ።...ከኛ ጥቂት ራቅ ብሎ 50ኛው ኪሎ ሜትር ላይ አምስት ሺ ወታደሮች መኖራቸውን ስንሰማ ደስ አለን ። ሞራላችንም ከፍ አለ ።....ሞጆ ከተማ ውስጥም ከኛ ጋር 400 ወታደር አለ ።....ከሰዓት በኋላ በመጀመሪያው ሰዓት 5 ሬሣዎች መጡ ። እነዚህም ሬሣዎች የካራቢኒየሪ ሻልሶቲ ሳልባቶሬ ፣ የ219ኛ ስኳድሮ አዛዥና በታላቁ ጦርነት የታወቀው ጀግና የሉኩሎ ታንጊን (Lucullo Tanghin) ፣ኤጂዲዮ ሳታ( Egidio Satta) የባቡሩ ገንዘብ ተቀባይ የእስጢፋኖስ ደስታና የካራቢኒየሪ መኩንን ነግሩ (Negru) ሬሣዎች ናቸው ። እነኚህንም ሬሣዎች ባንድ ቤት አኖሩዋቸው ። ....የዙቃላ አካባቢ አሁንም እየተደበደበ ነው ።....» ብሏል ።

የተጠናከረው የኢጣሊያ ጦር በሞጆና በቢሾፍቱ መሀል እየተዘዋወረ ሐዲዱን በሚጠብቅበትና የአካባቢውን ሰላማዊ ሰዎች በሚጨርስበት ጊዜ አርበኞቹ ሐምሌ 2 ቀን አዳማ (ናዝሬት) አጠገብ በባቡሩ ላይ አደጋ ጣሉ ። በዚህም አደጋ ጀኔራል ሜርካቲ ተገደሉ ። በዚህ ሁኔታ የተናደደው ግራዚያኒ በጀኔራል ጋሊና ላይ ሥጨበት ። በአስቸኳይ አርበኞቹን እንዲያጠፋም አዘዘው ። የኢጣሊያ ጦር በአስቸኳይ ወደ አዳማ እንዲሄድ ሲታዘዝ አርበኞቹ በዚያው ቀን ቢሾፍቱ አካባቢ ባለው ባቡር መስመር ላይ አደጋ ጣሉ ። ስለ ሐምሌ 2 ቀኑ ሞጆ የቀረው ፓጃሊ እንዲህ ይላል ።«....እንደገና ደግሞ ሽፍቶቹ አደጋ መጣላቸውን ሰማን።... ሽፍቶቹ በባቡሩ መስመር ላይ በሚጥሉት አደጋ የሞቱ 38 የኢጣሊያኖች ሬሣ መጣ።......»

ኢል ላ እኖ ዴል ኢምፔሮ የተባለው መጽሐፍ እንደሚለው ሐምሌ 3 ቀን ጀኔራል ጋሊና በአዳማ (ናዝሬት) አካባቢ ከባድ አሰሳ ሲያደርግ መዋሉንና በዚሁ ቀን የ3ኛው ሬጂሜንት የሊቢያ ባታሊዮን ደግሞ ሚኤሶ ባቡር ጣቢያ ላይ ቍሠፈረውን ጦር ለማጠናከር መላኩን ይገልፃል ።

ሐምሌ 4 ቀን 439 ኪሎ ሜትር ላይ አንድ ባቡር ተበላሽቶ ቆመ ። በዚህም ጊዜ አርበኞቹ ደርሰው በባቡሩ ላይ አደጋ ጥለውበታል ። የዚህም ባቡር የጥገና ሥራ አንድ ቀን ከግማሽ ከፈጀ በኋላ ተንቀሳቅሶ ጉዞውን ጀመረ ። አለቀለት ያሉት ባቡር ጉዞውን ሲጀምር ያዩት አርበኞች ሐምሌ 5 ቀን አደጋ ጥለውበት ብዙ ጉዳት አደረሱ ። ኢል.ላ.እኖ. ዴል. ኢምፔሮ መጽሐፍ ላይ እንደ ተገለፀው የዚህ ባቡር ሁለት ጐታቾችና 8 ጋሪዎች ተጐድተዋል ።

በዚሁ ቀን ማለት ሐምሌ 5 ቀን ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዝ አንድ ባቡር ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ ሞጆ አካባቢ ሲደርስ አርበኞቹ አደጋ ጣሉበት ። ስለዚሁ ቀን ሁኔታ ኢል.ላ.እኖ. ዴል. ኢምፔሮ መጽሐፍ ሲተርክ «....ሽፍቶቹ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ላይ በጣጥሰው የጣሉት የስልክ መስመር ተሠርቶ እንዳለቀ እንደገና ደግሞ 70 ኪሎ ሜትር ላይ ስልኩ ተበጣጥሶ ተገኘ...» ይላል ።

ስለ ሐምሌው 6 የቅዳሜውን ቀን ሁኔታ ፓጃሊ ሲገልጽ«....የሽፍቶቹን ኃይል በመፍራት ሞጆ ባቡር ጣቢያ ሰባት ቀን ተቀመጥን ። በዛሬውም ቀን የስምንት ኢጣሊያኖችና የሁለት ጥቁር ወታደሮች ሬሣ ሞጆ ከተማ ተቀበረ ። .....8 ሰዓት ተኩል (በኛ 2 ተኩል) ሲሆን ባቡራችን ከሞጆ ተነስቶ ጉዞ ጀመርን ። በመንገዳችን ላይ የምናየው ነገር ሁሉ በእሳት የተቃጠለ ነው ። ....» ብሏል ።

ሐምሌ 9 ቀን 1928 ዓ.ም. ቁጥር 238 የሆነው የጭነት ባቡር ከአዲስ አበባ ወደ ጂቡቲ ለመሄድ ከቀኑ ለአሥር ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ዱክም አጠገብ እንደደረሰ አርበኞቹ አደጋ ጥለውበት ከጉዞው አቋረጡት ። የኢጣሊያ ጦርም ተሰባስቦ በዚህ ባቡር ላይ አደጋ ያደረሱትን አርበኞች ለመያዝ በአካባቢው ላይ አሰሳ

ሲያደርግ አርበኞቹ በአካባቢው አልተገኙም ነበር ። የዚያን ጊዜ የዚያኑ ዕለት አርበኞቹ የነበሩት ሞጆ አካባቢ ነበር ። ኢጣሊያኖቹ የዱከምን አካባቢ ሲያስሱ ቁጥር 221 የሆነው የጭነት ባቡር በዚያው ሐምሌ 9 ቀን 28 ዓ.ም. ከቀኑ 11 ሰዓት ተኩል ሞጆ አካባቢ ሲደርስ አርበኞቹ በባቡሩ ላይ አደጋ ጥለው ከዱከም ወደ ሞጆ መዛወራቸውን አሳወቁ ።

አርበኞች ሠፍረውበታል ተብሎ የተጠረጠረው የደበጉጀና በካን ተራራዎች ሐምሌ 14 ቀን በጀኔራል ጋሊና የሚመራው ጦር በአይሮፕላንና በመድፍ ሲደበደብ ዋለ ። ኢጣሊያኖቹ ከዱከም እስከ አዳማ (ናዝሬት) ያለውን አካባቢ በሙሉ ወርረው በከባድና በቀላል መሣሪያ ሰላማዊውን ሕዝብ ሲደበድቡ ቦታቸውን የለወጡት አርበኞች ሐምሌ 23 ቀን ከአዋሽ ማዶ ባለው አርባ (ቦርደዴ) በሚባለው ባቡር ጣቢያ ላይ አደጋ ጥለው በዚያ ከሠፈረው የኢጣሊያ ሠራዊት ጋር ተዋግተው ተመለሱ ። ይህን በአርባ (ቦርደዴ) የደረሰውን አደጋ የሰሙት ጀኔራል ግራዚያኒ ሐምሌ 25 ቀን አንድ የተጠናከረ ተጨማሪ ጦር ቦርደዴ ጣቢያን እንዲጠብቅ ላኩ ።

ይህ ወደ ቦርደዴ የተላከው ጦር አደጋ የጣሉትን አርበኞች ለማጥፋት በአካባቢው ከባድ አሰሳ ቢያደርግም አርበኞቹ ሊገኙ አልቻሉም ። የቦርደዴ አካባቢ አሰሳ በሚደረግበት ጊዜ አርበኞቹ ወደ አንኮበር ተሻግረው ነበር ። አርበኞቹ በአንኮበር ስምንት ቀናት ያህል ቆይተው የተጠናከረውን የቦርደዴን ጠላት ትተው ነሐሴ 7 ቀን 1928 ዓ.ም. አዋሽ ባቡር ጣቢያ የሠፈረውን ጀኔራል ቴሲቶሬ በሚመራው ጦር ላይ አደጋ ጣሉ ። ኤል.ላ.አና. ዴል.ኢምፔሮ መጽሐፍ እንደሚገልጸው አርበኞቹ በጀኔራል ቴስቶሬ ጦር ላይ ጉዳት አድርሰዋል ።

ቦርደዴ ላይ የሰፈረው የኢጣሊያ ጦር የተጠቃውን የአዋሹን ጦር ለመርዳት እለቱኑ በግሥጋሴ አዋሽ ደርሶ በማግሥቱ ነሐሴ 8 ቀን አሰሳ ሲያደርግ ዋለ ። አርበኞቹ ግን አልተገኙም ። እንደገና ነሐሴ 9 ቀን አርበኞቹን ፍለጋ የኢጣሊያ ጦር የአዋሽን አካባቢ ሲያስስ አርበኞቹ መተሃራ ከሚባለው ባቡር ጣቢያ ላይ አደጋ ጥለው ከጀኔራል ቴ[illegible]ሬ ወታደሮች ገዳድለው ተመለሱ ። አሳቹ የኢጣሊያ ጦር ደርሶ በመተሐራ አካባቢ አሰሳ ሲጀምር በማግሥቱ ነሐሴ 10 ቀን አርበኞቹ መልክጂሎ ከሚባለው ባቡር ጣቢያ ላይ አደጋ ጣሉ ።

ስለዚያን ጊዜው ሁኔታ ጋዜጠኛው ቺሮ ፖጃሌ እ.ኤ.አ. ነሐሴ 26 ቀን (በኛ 20) በያዘው ማስታወሻ “......በሐዲዱ አካባቢ ያሉትን ሽፍቶች ለማሰስ ከሄዱት ወታደሮች መሀል 27 ወታደሮች ተገደሉ ።.....እነኚህንም ሽፍቶች በበላይነት የሚመሩት የሰማንያ ዓመቱ ሽማግሌ ደጃች ባልቻ ናቸው......” ብሏል ።

ነሐሴ 22 ቀን አርበኞቹ ከ203 እስከ 205 ኪሎ ሜትር ባለው ስፍራ አድፍጠው ለእርዳታ ወታደሮች የጫነ ባቡር ሲሄድ አደጋ ጥለውበት ከባድ ጉዳት አደረሱ ። በማግሥቱም ነሐሴ 23 ቀን ቀበሌው በኢጣሊያ ወታደሮች ሲደበደብ ዋለ ። ጠላትን ግራ የሚያጋባውን ይህን የአርበኞች ዘዴ የሚመሩት ደጃዝማች ባልቻ ናቸው ተብሎ በጠላት ዘንድ ተረጋገጠ ። በተለይ ነሐሴ 20 ቀን ደጃች ባልቻ በተጠናከረ ኃይል የአዲስ አበባ ከተማን አይሮፕላን ማረፊያ ካጠቁ ወዲህ ኢጣሊያኖች ደጃች ባልቻ አሉበት የሚባለውን አካባቢ ሁሉ የተጠናከረ ጦር እየላኩ ይደበድቡ ጀመር ።

1ኛ እና 7ኛ ብርጌድ የኢጣሊያ ጦር ደጃች ባልቻ አሉበት ወደተባለው ወደ ቱሪና ወደ ወጨጫ ተልኮ ነሐሴ 26 እና 27 ቀን አካባቢውን ሁለት ቀን ሙሉ ሲደበድብ ዋለ ። አርበኞቹም ሆኑ ደጃች ባልቻ አልተገኙም ። ኢጣሊያ ደጃዝማች ብሎ የሾማቸው የባንዳ ተከሉ ወታደሮችና የራብ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ወታደሮች በሕብረት ሆነው በባቡሩ ሐዲድ አካባቢ ግራ ያጋባውን የደጃች ባልቻን ጦር ለመደም

ለስ ወደሚታ ሔደው መስከረም 1 ቀን 1929 ዓ.ም. ከደጃች ባልቻ ጦር ጋር ገጥመው ድል ሆነው ተመለሱ ። ጋዜጠኛው ቺሮ ፖጂሌ እንደገለፀው ራስ ኃይሉ ወታደር የሚያደራጁበትና ለወታደሮቻቸው ደሞወዝ የሚከፍሉት በየወሩ አንድ መቶ ሺ ሊሬ ከኢጣሊያ መንግሥት ይሰጣቸው ነበር ።

በከዳተኛ ያገር ተወላጅም ሆነ ከውጭ በመጡ ኢጣሊያኖችና የቅኝ ግዛት ወታደሮች በዘመናዊ መሣሪያ ቢደበደብም የአርበኞቹ ኃይል ተዳክሞ በባቡሩ መንገድና በባቡሩ ላይ የሚያደርሱት አደጋ አላቆመም ። የሚገርመው ነገር አርበኞቹ የኢጣሊያን እንቅስቃሴ በየቀኑ መቆጣጠራቸው ነው ። የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ሚኒስትር የሆኑት ሌሶና ለጉብኝት ወደ አዲስ አበባ በመስከረም ወር ይመጡ ነበር ። ጀኔራል ግራዚያኒ ጊዜው አደገኛ በመሆኑ ሚኒስትሩ በቀጥታ በአይሮፕላን አዲስ አበባ እንዲገቡ በማለት አሳብ ቢያቀርብ ሌሎቹ መኳንንቶች "እንዴት ጦርነቱ ቆሟል ካልን በኋላ ሽፍቶቹ መኖራቸውን እናሳውቃለን? የሽፍቶቹም ኃይል ተዳክሟልና ነገሩ ስለማያሰጋ የቅኝ ግዛት ሚኒስትሩ ቅኝ ግዛት አገራቸውን እያዩ በባቡር ይምጡ" በሚል አሳብ ስላሸነፉ የሚኒስትሩ ጉዞ በባቡር እንዲሆን ተወሰነ ። ሚኒስትሩን የያዘው ባቡርም ከጂቡቲ ከምሽቱ 1 ሰዓት ተነስቶ ከጧቱ 3 ሰዓት ድሬዳዋ ገባ ።

የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ሌሶናን የያዘው ባቡር ከምሽቱ 3 ሰዓት ከድሬዳዋ ከመነሳቱ በፊት በሙሉ ትጥቅ ወታደሮችን የጫነ ባቡር ቀደመ ። ሌሶናን የያዘው ባቡር ተከተለ ። ከኋላ ደግሞ ሙሉ ትጥቅ ያላቸው ወታደሮች ያሉበት ባቡር ተከተለ ። የዚህ ጉዞ ሁኔታ ወሬው ለአርበኞቹ ደረሰ ። መስከረም 30 ቀን 1929 ዓ.ም. የመጀመሪያው ባቡር ከዱከም ከተማ አራት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ እንዳለ ማለት 442 ኪሎ ሜትር ላይ ከቀኑ 7 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ሲሆን በባቡሩ ላይ አደጋ ጥለው ሸሹ ። አርበኞቹ የመጀመሪያው ቀዳሚ ባቡር ሚኒስትሩ ያሉበት መስሏቸው ነበር ። ሌል.ላ.እኖ. ዴል ኤምፔሮ መጽሐፍ በዚያ ቀን አደጋ የጣሉትን አርበኞች ዲያቦሎ (ሰይጣኖች) ይላቸዋል ። ፖጂሊም በያዘው ማስታወሻ "....በአቃቂና በዱከም መሀል ባለው የባቡር መንገድ ላይ እንደገና አደጋ ተጣለ ። ይህ አደጋ የተጣለው የኢጣሊያ የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ሌሶና እና ሚኒስትር ኮቦሊ ጂሊ (Cobolli Gigli) ያሉበት ባቡር ከመድረሱ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ነው ። ........አደጋው ከደረሰበት ባቡርም ውስጥ ስምንት ኢጣሊያዊ ወታደሮች ሞተዋል ።......." ይላል ።

የአርበኞቹ አድራጎት የጥበቃውን ኃላፊነት የያዙትን ግራዚያኒን ብቻ ሳይሆን መላውን ኢጣሊያና የኢጣሊያ ወታደርን ሁሉ ግራ አጋባ ። በሚኒስትሩ ባቡር ላይ አደጋ የጣሉት አርበኞች ኤረር ተራራ መሽገዋል ስለተባለ ኤረር ተራራ በአይሮፕላን እና በመድፍ ከጥቅምት 1 ቀን ጀምሮ ሲደበደብ ከረመ ። ከተራራው በኩል የመልስ ተኩስ ስለጠፋ ጥቅምት 5 ቀን እግረኛ የኢጣሊያ ጦር ተራራውን ማሰስ ጀመረ ። አርበኞቹ ግን አልነበሩም ። የኢጣሊያ እግረኛ ጦር አርበኞቹ አሉበት የተባለውን ኤረር ተራራን ጥቅምት 5 ቀን ሲያስስ፣ አርበኞቹ በዚያው ዕለት ናዝሬት አጠገብ በባቡር ላይ አደጋ ጥለው ናዝሬት አካባቢ መሆናቸውን አሳወቁ ። የባቡሩን መስመር ጥበቃ ኃላፊነቱን የወሰዱት ጀኔራል ግራዚያኒ ከጥቅምት 5 ቀን በኋላ በአርበኞቹ የጦር ታክቲክ መሸነፋቸውን አመኑ ። ኃላፊነቱን የሚችል ሰው ተመርጦ ጀኔራል ጋሊና (Gallina) ተሾመ ። ጀኔራል ጋሊናም ሹመቱን በደስታ ተቀብሎ አርበኞቹን ለማጥፋት ሹመቱን ተቀብሎ ወጣ ሲል ጓደኞቹ እንኳን ደስ አለህ ሲሉት አንድ ወታደር ደብዳቤ ሰጠው ። ደብዳቤው የተጻፈው ስለባቡር አደጋ ነበር ። "...ወታደር የጫነው ባቡር፣ 380 ኪሎ ሜትር 12ኛው የስልክ ብረት ከተተከለበት አጠገብ ዛሬ ጧት በ1 ሰዓት ሲደርስ አደጋ ተጥሎበት ጉታቹና 3 ጋሪዎች ተሰባብረዋል...." የሚል ነበር ። ጀኔራል ጋሊናም "ሽፍቶቹ እየታደኑ በሰፊው እንዲገደሉ" ሲል አዘዘ ።

ጀኔራል ጋሊና የአበባውን ትእዛዝ ሰጥቶ ወታደሩ ዕለቱኑ ማለት ጥቅምት 5 ቀን ለአበሳ ተሰማራ ። በማግሥቱ ጥቅምት 6 ቀን ጀኔራል ጋሊና ከቢሮው ሆኖ ለአሰሳ ከተሰማራው ወታደሩ "ሽፍቶቹ ተደምስሰዋል" የሚል መልስ ሲጠባበቅ በምትኩ "....ሽፍቶቹ በሞጀና በአድአ መሀል ያፈራረሱት 200 ሜትር ርዝማኔ ያለው ሀዲድ ተጠግኖ አልቋል ። ይህ ሥራ ማለቁ ቢያስደስትም እነኚህ የሰይጣን ቁራጭ የሆኑት ሽፍቶች ዛሬ ጥቅምት 17 ቀን (በኛ ጥቅምት 6 መሆኑ ነው) በአዋሽና በውሊንጪቲ መሀል አደጋ ጥለው በባቡሩ ላይ ጉዳት ደርሷል ።....." የሚል የቴሌግራም ወረቀት ደረሰችው ። ጀኔራል ጋሊናም ጦሩ በአስቸኳይ ወደ አዋሽና ውሊንጪቲ እንዲሄድ አዘዘ ። አይሮፕላኖችም ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ እየተነሱ አደጋ የደረሰበትን አካባቢ እንዲደበድቡ ታዘዙ ። ያም አካባቢ ጥቅምት 7 ቀን 29 ዓ.ም. ሲደበደብና ሲታሰስ ዋለ ።

አርበኞቹም ቢሆኑ ጥቅምት 7 ቀን ሥራ ፈትተው አልዋሉም ። የኢጣሊያ ጦር የአዋሹን አካባቢ ሲደበድብ ከአዲስ አበባ ወደ አዋሽ ለድብደባ የተላከውን ወታደር የጫነው ባቡር ውሊንጪቲ ሲደርስ ቆመ ። ምክንያቱም አርበኞቹ ጥቅምት 7 ቀን በውሊንጪቲና በቦርጮታ መሃል 399 ኪሎ ሜትር ላይ ሐዲዱን ሰባብረውት ስለነበር ባቡሩ ሊያልፍ አይችልም ነበርና ነው ። ለሊቱኑ ሚሊሽያው ወታደር ሐዲዱን ጠግኖ ጨርሶ ባቡሩ ጉዞውን ጀመረ ። በባቡር የተጫነው ወታደር እንዳለፈ አርበኞቹ ከአዋሽ 74 ኪሎ ሜትር ላይ የስልኩን መስመር በጣጠሱት ። ኤል ላ. እና. ዴል ኤምፔሮ መጽሐፍ "......ይህን የተበጣጠሰውን የስልክ መስመር 106 ሠራተኞች ተልከው ሠሩት ።...."ይላል ።

ጥቅምት 7 ቀን የተፈጸመው ድርጊት ይህ ብቻ አይደለም ። የጀኔራል ጋሊና ጦር የአዋሽን አካባቢ ሲደበድብና ሲያስስ በአዋሽና በውሊንጪቲ መሀል አደጋ ተጥሎበት የነበረውና ያመለጠው ባቡር ከቢሾፍቱ ከተማ ወጣ ሲል አርበኞቹ አደጋ ጣሉበት ። የጀኔራል ግራዚያኒን ራስ ያዞረው የባቡር ላይ አደጋ ጣይ አርበኞች ሥራ፣ የጀኔራል ጋሊናንም ራስ ያዞረው ጀመር ። ጋዜጠኛው ፖጃሊ እ.ኤ.አ. ኦቶብሬ 18 (በኛ ጥቅምት 7) ቀን በያዘው ማስታወሻ ".....በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ እና በአዳለ (ቢሾፍቱ) መሀል በባቡር ላይ አደጋ መድረሱን ሰማን ።.... ባቡሩ የተመታው በመድፍ ነው ። በባቡሩ ውስጥ ካሉት ጠባቂዎች 6 ወታደሮች ሲሞቱ ጉታቹ (ሉኮሞቲቩ) ግን ፈጽሞ ተሰባብሯል ።...."ብሏል ።

አርበኞቹ ብዙውን ጊዜ የሚያጠቁት የዕቃ መጫኛ የሆነትን ባቡሮች ነበር ። ይህም ኢጣሊያኖች ርዳታ እንዳያገኙ ለማድረግ ነበር ። አደጋ በሚጥሉበት ባቡር ላይ ሁሉ የሚኙት ቁጥር የሚያንሰው በየባቡሩ ላይ የሚገኙት ባቡሩን የሚጠብቁ ጥቂት ወታደሮች ብቻ በመሆናቸው ነው ።

ይሻላሉ ተብለው ለባቡሩ ጥበቃ በግራዚያኒ ቦታ የተተኩት ጀኔራል ጋሊና ተበሳጩ ። አድአና የዱከም አካባቢ በተጠናከረ ኃይል በማያዳግም ሁኔታ እንዲደበደብ አዘዙ ። አርበኞቹ ግን ጥቅምት 7 ቀን በዱከም አካባቢ ደግሞ 130 ሜትር ርዝማኔ ያለውን ሐዲድ አወላልቀው ጥለውት ስለነበር በአስቸኳይ ሐዲዱን የሚሠራ ሠራዊትም ተላከ ። አሳሹ ጦር ባላገሩን ሲደበድብ አርበኞቹ ሐዲድ ሠራተኞቹ ዘንድ መጥተው እንደ ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ እንደ ፖጃሊ አመስካከር 17 ሐዲድ ሠሪ ኢጣሊያኖችን ገደሉ ። በዚህ ድንጋጤም የሐዲዱ ጥገና ሥራ 5 ቀናት ፈጀ ።

በቢሾፍቱና በዱከም መሀል ያለው ሐዲድ ጠባቂ የኢጣሊያ ጦር፣ አርበኞቹን ወደ ሐዲዱ አላስጠጋ አለ ። የሐዲዱ ሥራም በእንዲህ ዓይነት ጥበቃ ጥቅምት 12 ቀን ተሠርቶ አለቀ ። የሐዲዱ ሥራ አልቆ ባቡሩ ሥራ ለመጀመር ከአዋሽ ጧቢያ ጥቅምት 12 ቀን ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዘ ውሊንጪቲ አጠገብ ጉማ ቡታ

በተባለ ቦታ ሲደርስ አርበኞቹ አደጋ ጣሉበት ። ጥቅምት 13 እና 14 ቀን እላሽ የኢጣሊያ ጦር ተልኮ ውሊንጪቲን እስሶ መንገዱ ነፃ መሆኑን አሳወቀ ። ጥቅምት 15 ቀን ከአዋሽ የተነሳ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ለማምራት ከከተማዋ ወጣ እንዳለ በአርበኞች አደጋ ተጣለበት ። ኃይለኛ የኢጣሊያ ጦርም ጥቅምት 16 ቀን ለአሰሳ ሲወጣ አርበኞቹ ተኩስ ከፍተው ጦሩን ወደ መጣበት ወደ አዋሽ ከተማ መለሱት ።

በዚሀ ሁኔታ የአርበኞቹ ግራ ማጋባት እየተጠናከረ በመሄዱ ኢጣሊያኖቹ የተለየ ቋሚ የጥበቃ ዘዴ አበጁ ። ጥበቃው በሶስት መደብ የተከፈለ ነበር ። አንደኛው ቡድን ፣ ከአዲስ አበባ እስከ አዋሽ ያለውን መንገድ ፣ 2ኛው ቡድን ደግሞ ከአዋሽ እስከ ድሬዳዋ ያለውን መንገድ ሲጠብቅ ፣ 3ኛው ቡድን ከድሬዳዋ እስከ ወሰናችን እስከ ደወሌ ድረስ የሚጠብቅ ነበር ። ለዚህም የጥበቃ ሥራ 72 ከፍተኛ መኰንኖች፣ 113 ዝቅተኛ መኰንኖች ፣ 1136 ወታደሮችና 81 ሲቪል ሠራተኞች ተመድበው ነበር ። በያንዳንዱ ቡድን ያለው የጥበቃ አባል ሥራ ያለማቋረጥ በባቡሩ መስመር ላይ እየተመላለሰ ሐዲዱን መቆጣጠርና መጠበቅ ነበር ። በዚህም የጥበቃ ዘዴ የባቡሩ አደጋ ፋታ አገኘ ።

——O——

## ፲ ፱ ፻ ፳ ፱

ለንደን ከተማ ያለው የኢትዮጵያ ለጋሲዮን መስከረም 11 ቀን አንድ መግለጫ አወጣ ። «....ከኢትዮጵያ ግዛቶች ሁለት ሶስተኛው በኢጣሊያኖች አልተያዘም ። 36 አውራጃዎች ጨርጨር ፣ ባሌ ፣ አሩሲ ፣ ከምባታ ፣ ወላሞ ፣ ገሙጐፋ፣ ኮንታ ፣ ከፋ ፣ ጐልዲያ ፣ ሸዋ ጊሚራ ፣ ጎራ ፣ ኩሎ ፣ ሊሙ ፣ ጉማ ፣ ጂማ ፣ ጉራጌ ፣ ሰዮ ፣ ጐሬ ፣ ኖኖ ፣ በኒሻንጉል ፣ ለቀምት ፣ ሲቡ ፣ ጨልያ ፣ ጥብዬ ፣ ጥቁር ምድር ፣ ግንደ በረት ፣ ሜጫ ፣ ሰላሌ ፣ መርሀቤቴ ፣ ደራ ፣ ቦረና ፣ ሰዶ ፣ አዳል እነኚህ ሁሉ በኢጣሊያኖች አልተያዙም ።....የኢትዮጵያ ወታደር እስካሁን ድረስ በጦር ሜዳ ላይ ነው ። ራስ ደስታ በሲዳሞ ፣ ደጃዝማች በየነ መርዕድ በባሌ ፣ ደጃዝማች አበራ ካሣ ደግሞ በሰላሌ ሆነው ይዋጋሉ ። እነኚህ ሁሉ ጐሬ ባለው ጠቅላይ ጦር ሠፈር በራስ እምሩ የሚታዘዙ ናቸው ።.....» የሚል ነበር ።

ጂቡቲ ተቀማጭ የሆነው የኢትዮጵያ ዜና ተከታታይ መስከረም 12 ቀን የሚከተለውን ሪፖርት ወደ ለንደን አስተላለፈ ። «....በአዲስ አበባና በአሰበ ተፈሪ ከተማዎች ባለፉት ሁለት ሣምንታት ፀጥታው የበለጠ እየደፈረሰ ሄዷል ። ....ጳጉሜ 5 ቀን በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ታላቅ ውጊያ ተደርጓል ። መስከረም 5 ቀን አንዲት ሆስፒታል ያላት መርከብ ጂቡቲ መጣች ። እኛም እንደ ገመትነው ይህች የሆስፒታል መርከብ የመጣችው ከኢትዮጵያ የሚመጡትን ቁስለኞች ለመውሰድ ነው ። በዚያኑ ዕለት ምሽትም 4 ሰዓት ተኩል ሲሆን ሁለት መቶ ቁስለኞች በልዩ ባቡር ተሳፍረው መጡ ። በማግሥቱ መስከረም 6 ቀን ደግሞ ከምሽቱ 4 ሰዓት ሲሆን በልዩ ባቡር ተጭነው 310 ቁስለኞች መጡ ። መስከረም 7 ቀን የመጣው 3ኛው ባቡር 533 ቁስለኞች ይዞ መጣ ። ያቺም መርከብ ሁሉንም ጭና መስከረም 8 ቀን ጉዞዋን ቀጠለች ። ከኢጣሊያ አገር የሚመጡት የኢጣሊያ ወታደሮችና ከኢትዮጵያ የሚመለሱ ኢጣሊያኖች ጂቡቲ ሲደርሱ ፈጽሞ እንዳይገናኙ ይደረጋል ።

«.....ኢጣሊያኖች ከሶማሌ ቅኝ ግዛታቸው 14.000 የሶማሌ ወታደሮችን ወደ ኢትዮጵያ አስገብተው ነበር ። እነኚህም በየቦታው በተደረገው ጦርነት አልቀው አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ በሕይወት ያሉት የሶማሌ ወታደሮች 3.000 ያህል ናቸው። ዛሬ በኢጣሊያ ሶማሌ ውስጥ ያሉ እናቶች በሁሉም ቦታ በማልቀስ ላይ ናቸው ።..»

የክረምቱ ወራት ቀለል እንዳለ አርበኞች በየቦታው ውጊያቸውን ቀጠሉ ። መስከረም 8 እና 10 ቀን በሐረርጌ ክፍለ አገር ቁሉቢ ላይ ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ ። መስከረም 15 ቀን ደግሞ ደብረሲና በተደረገው ጦርነት አርበኞች በኢጣሊያ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ ። በሰሜን ባሉ የሸዋ አርበኞች መሀል ጭቅጭቅ ይነሳ እንጂ ሌላው የሸዋ አርበኛ ኢጣሊያን ክፉኛ አስጨንቆ ነበር ።

በጥቅምት ወር በመላው ኢትዮጵያ ያሉ አርበኞች 173 የኢጣሊያ መኰንኖች ፣ ወታደሮችና መንገድ ሠሪዎችን ገደሉ ። ይህ ቁጥር ራሳቸው ኢጣሊያኖቹ ያመኑት ሲሆን ጥቁሩን ወታደር አልጨመረም ። በዚያን ጊዜው የአገር ውስጥ ውጊያ ኢጣሊያኖቹ የሚያዋጉት እርስ በርሱ ጥቁሩን ከጥቁር በመሆኑ ወዳንድ አቅጣጫ ለሚዘምት ጥቁር የኢጣሊያ ጦር ፣ አዝማቹ ብቻ ኢጣሊያዊ እየተደረገ ነበር ። በዚህም መሠረት በአንድ ወር ውስጥ 173 ኢጣሊያውያንን መግደል ቀላል ነገር አይደለም ።

በዚህ በጥቅምት ወር 1929 ዓም ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አባተሜን ተገደሉ ። ጋዜጠኛው ቺሮ ፖጃሊ 29 ኦቶብሬ 1936 ጆቬዲ (ሐሙስ) በሚለው ርእስ ሥር በያዘው ማስታወሻ«.....ፍቅረ ማርያም በሐዲዱ አካባቢ ተገደሉ ...» ይላል። 2 ኖቬምቤር 1936 ሉኔዲ (ሰኞ) በሚለው ርእስ ሥር ደግሞ«.....አንድ አስከሪ (ጥቁር ወታደር) የፍቅረ ማርያምን ራስ ቆርጦ ወደ አዲስ አበባ አመጣ ። የሚያውቋቸው ሰዎች ተሰብስበውም እሳቸው መሆናቸውን አረጋገጡ ። የተገደሉትም ከባቡሩ ሐዲድ አጠገብ ነው ። .....» ይላል ። ገድሎ ራሳቸውን ቆርጦ ላመጣው ጥቁር ወታደር በአዋጁ መሠረት አስር ሺ ሊሬ እንደተሰጠውም ይገልፃል ። ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም የተገደሉት ኤረር ተራራ አጠገብ ሉች በተባለች ቦታ እንደሆነ ፖጃሊ ይገልፃል ። ፖጃሊ 8 አፕሪሌ 1937 ጆቬዲ (ሐሙስ) በሚል ርእስ ሥር በያዘው ማስታወሻ«...ፍቅረማርያም የሞቱባትን አሩሲ ውስጥ (ኤረር አቅራቢያ) ያለችዋን ሉቼ (Luc) የተባለችውን መንደር ለማየት ሄድን ።...» ይላል ።

ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶም በዚሁ በጥቅምት ወር 1929 ዓም ተገደሉ ። ያው ጋዜጠኛ ፖጃሊ ስለደጃዝማች ባልቻ አሟሟት 7 ኖቬምብሬ 1936 ዶሜኒካ (እሁድ) በሚለው ርእስ ሥር በያዘው ማስታወሻ«....ከአምቦ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ደጃች ባልቻ መገደላቸውን ሰማሁ ። እኚህ የሰማንያ ዓመቱ ሽማግሌ በዚህ ዕድሜያቸው በመሸፈታቸው ከሌሎች ሁሉ የተለዩ ብርቅ ነበሩ ።...» ይላል ።

ኢጣሊያኖችም የባቡር ሀዲድ ያለበትን አካባቢ ሁሉ በመርዝ ጭስና በቦምብ አስደበደቡት ። በአካባቢው ሲዘዋወር የተገኘ ሁሉ እየተያዘ በጥይት ይደበደብ ጀመር ። በቁጥር 1092 ለግራዚያኒ በተላከለት ቴሌግራም «.....ከሽፍቶች መካከል ዛሬ ጥቂቶችን ማርከናል ። 1/ ወልደመድኅን መስቀሉ ፣ 2/ ኃይሉ መርሻ ፣ 3/ ፈይሣ ሳተና ፣ 4/ ሽሪፍ ሺሞ ፣ 5/ ወልዱ ስነ ገብርኤል ፣ 6/ ፈለቀ ማናግዶት የተባሉት ሰዎች ከዱከም አዳማና ሞጆ ባለው ቀበሌ የተማረኩ ሲሆኑ በጥይት እንዲደበደቡ አዝዤ የጥይቱ ድብደባ ዛሬ ጥቅምት 12 ቀን ተፈጽሞባቸዋል ...» በማለት ጀኔራል አርኪሜዲ ሚስኪ አስታውቋል ።

ግራዚያኒም በሚስጢር ቁጥር 22104 በመላ ኢትዮጵያ ላሉ ለኢጣሊያ ባለሥልጣኖችና ለቅኝ ግዛት አገሮች ሚኒስትር ቴሌግራም ሲያስተላልፍ «.....በፒና አዛዥነት አየር ኃይላችን ዛሬ ጧት የዘቋላን ተራራና አካባቢውን ሁሉ እንዲመታ አዝዤ ስለነበር በሞጆና በአዳማ አካባቢ ያለው አገር ሁሉ በሚገባ ተደብድቧል ። በዚህም ድብደባ 25 አይሮፕላኖች ተካፋይ ሲሆኑ አስሩ ቦምብ ጣይ ናቸው ።.... በመጨረሻም በጠቅላላው በቀበሌው ላይ መርዝ ጋዝ ተረጭቶባቸዋል ።...» ብሏል ።

ሌላው አርበኛ በያለበት ፤ ባለው አቅም ሲከራከር በሸዋ ግን በአርበኞች መሀል ጭቅጭቁ እየቀጠለ ሄደ ። ደጃች አበራ ካሣም ፣ አርበኞች ለኢጣሊያ እጃቸውን እን

ጊሰጡ ይጐተጉቱ ጀመር ። በተለይ በዚያን ዘመን ተከታዮቻቸውን እያበረከቱ የሄ
ዱት በዘመኑ ባላምበራስ ፥ በኋላ ራስ የተባሉት አበበ አረጋይ ስለነበሩ ደጃች አበራ
ካሣ ከአበበ አረጋይ ጋር በመጻጻፍ እጃቸውን እንዲሰጡ ይመክሩዋቸው ጀመር ።
ከውጭ ቋንቋ የተረጐምኳቸውን ጥቂቶቹን ደብዳቤዎች እንመልከት ።

ይድረስ ከባላምበራስ አበበ አረጋይ

እንደምን ሰንብተሃል ። እግዚአብሔር ይመስገን እኛ ደህና ነን ። ከንጉሠ
ነገሥቱ የምንጠብቀው እርዳታና የማኅበሩም ውሳኔ እንደምንጠብቀው ፈጥኖ እስ
ካሁን ድረስ አላደረሰንም ። የምንፃፃፈው ሁሉ ፍሬቢስ ሆነ ። ስለዚህ ዕርዳታው
ጊዜ የሚወስድ ከሆነ የሚሻለው ነገር ከኢጣሊያ ጋር ያለመዋጋቱ ነው ። አሁን
ውጊያውን ብንጀምር የኢጣሊያ ጦር ይወረናል ። ይህን ወረራ ለማቆምና ኢጣሊያኖ
ችም እንዳይጐዱን በማለት እኔና በዙርያዬ ያሉ መኳንንቶች ጥቂት ስጦታ ልከ
ንላቸዋል ። ይህም ለወደፊት ጠቃሚ ስለሆነ አንተና ዙርያህን ያሉ ሌሎች መኳ
ንንቶችም እኛ እንዳደረግነው አድርጉ ።

ደጃዝማች አበራ ካሣ ።

ደጃዝማች አበራ ካሣ ይህን በሚያስቡበት ጊዜ አበበ አረጋይ ሥራ ላይ ነበሩ።
ግንቦት 25 ቀን ደንባ ላይ ፥ ጥቅምት 5 ቀን ጫጫ ላይ ፥ ጥቅምት 6 ቀን ሳላይሽ
ላይ ፥ ኅዳር 4 ቀን ዝንጀሮ ሜዳ ላይ ከጠላት ጦር ጋር ገጥመው በጠላት ላይ ብዙ
ጉዳት አድርሰዋል ። የደጃዝማች አበራ ደብዳቤ እንደ ደረሳቸውም መልሱን ጻፉ ።

ይድረስ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ።

መድኃኒዓለም ጤና ይስጥልኝ እያልኩ እጅ እነሳለሁ ። ወደ ደንባና ቈደፍቼ
ከሚሄደው ጠላት ጋር ዝንጀሮ ሜዳ ላይ ገጥሜ ድል አደረግሁት ። ብዙ የጦር
መሣሪያና መድፍ በመማረኬም ደስ ብሎኛል ። አሁን እንግዲህ ጠላትን ብዙ ጊዜ
ድል ካደረግሁት በኋላ እንዴት አድርጌ ስጦታ ልላክለት ። እንዴትስ አድርጌ ከይ
ቅርታህ ሥር ነኝ ልበል ። እንድልክለት የጠየቁኝ ስጦታ ለኔ ብዙ ወጭ የሚች
ልልኝ ነው ። ደግሞም ስጦታ ብንልክና በሱ ሥር መሆናችንንም ብናስታውቅ ኢጣ
ሊያ ኑና እንገናኝ ማለቱ ይቀራል ወይ ። ባንሄድና ባንገናኝ ደግሞ በጦር ኃይል
ይመታናል ። ስለዚህ በኔ በኩል ገንዘባችንን ማባከን አልፈልግም ። ደብዳቤዎ እን
ደደረሰኝ በሰዎቼ መሀል ክርክር ፈጥሮአል ። እነሱም እንደሚከተለው ጠየቁኝ።
እንድነት ሆነን እንዋጋለን ካልን በኋላ ለምንድነው አበራ የኢጣሊያን መንግሥት
የተቀበሉበት ምክንያት እያለ ይነጋገራል ። ኢጣሊያኖችን ለማብረድ እርስዎ ለኢ
ጣሊያኖች ግብር ቢሰዱ ወታደሩ በሁለታችን መሀል ልዩነት መኖሩን ይረዳዋል ።
ስለዚህ በሁለታችን መሀል የዓላማ ልዩነት ያለመኖሩን ለማሳየት ይዘዙኝና ከሰ
ዎቼ ጋር መጥቼ ለእርስዎ ግብር ልገብርልዎ ። እኛም ከዚያ በምንመጣበት ጊዜ
ሰዎቼን ማነቃቂያ ምክር ይመክሩልኛል ።

አበበ አረጋይ

* * *

ይድረስ ከባላምበራስ አበበ አረጋይ

እንደምነህ ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ ። ደብዳቤህ ደረሰልኝ ።
ዝንጀሮ ሜዳ ያገኘኸውን ድል ስሰማ ደስ አለኝ ። እኔ መጥቼ ካንተ ጋር ለመገ
ናኘት የማይቻለኝ ነገር ነው ። ስለዚህ አንተ ብትመጣ ይሻላል ። ነገር ግን ግብር

ልትገብርልኝ ከሰዎችህ ጋር መምጣትህን አልፈልግም ። እንደ ነገርኩህ ለኢጣሊያኖች ስጦታ ልኬአለሁ ። አሁን የጦር ግብር ለመገበር ከሰዎችህ ጋር ወደኔ ብትመጣ ኢጣሊያኖች ከኋላ እንደምወጋቸው አድርገው ያስቡታል ። አሁንም የሰላም ንግግር ጀምረናል ። ነገር ግን ብቻህን ብትመጣ በሁሉም ነገር ላይ እንነጋገርበታለን ።

ደጃዝማች አበራ ካሣ

በደጃዝማች አበራ ካሣ ጥያቄ መሠረት ባላምበራስ አበበ አረጋይ ወደ ደጃዝማች አበራ ካሣ አልሄዱም ። ያልሄዱበትም ምክንያት በውስጣቸው ያሉ ጦር አዛዦች መሄዳቸውን ስለተቃወሙ ነው ። ወዲያው ደግሞ በጄኔራል ትራኪያ ( Tracchia) የሚመራ የጠላት ጦር ወደፍቼ ለማለፍ በአበበ አረጋይ በኩል መምጣቱም ስለተሰማ ነው ። ስለዚህ ራስ አበበ ዕርዳታ ለመጠየቅ ወደ ደጃች አበራ ደብዳቤ ጻፉ ። ራስ አበበ ራስ የተባሉት ከዚያው ከዱር በአርበኝነት ሜዳ በሠራዊቱ ምርጫና ፍላጐት ነው ። በኋላ ግን ንጉሠ ነገሥቱ አፅድቀውላቸዋል ።

ይድረስ ከክቡር ደጃዝማች አበራ ።

መድኃኔዓለም ጤና ይስጥልኝ እያልኩ እጅ እነሳለሁ ። ባለፈው ጊዜ በጻፍኩሎት ደብዳቤ ፈቃድዎ ሆኖ ከነሰዎቼ ወደእርስዎ እንድመጣ ጠይቄዎ ነበር ። እርስዎ ግን ፈቃድዎ ባለመሆኑ ሰዎቼን በብዙ አበሳጫቸው ። አሁን እንደሰማሁት ጄኔራል ፉጂሪ ትራኪያ ኅዳር 19 ቀን ከደብረብርሃን ተነስቶ እኛን ለማጥቃት ይመጣል አሉ ። ጄኔራል ትራኪያን ለመዋጋት በቂ ወታደር አለኝ ። ነገር ግን እርሶ ከኛ ጋር መሆንዎን ለሠራዊቱ ለማሳየት አንድ መቶ ያህል ሰዎችና አንድ መድፍ ለእርዳታ ብለው ቢልኩልኝ እጅግ በጣም ጥሩ ነገር ይሆናል ። እኛ መተላለፊያውን መንገድ ከለቀቅንለት ቀጥሎ የሚያጠቃውና የሚመታው እርስዎን መሆኑን ይወቁት ።

ራስ አበበ አረጋይ

* * *

ይድረስ ከባላምበራስ አበበ አረጋይ

እንደምነህ ። እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደህና ነኝ ። ደብዳቤህ ደረሰልኝ ። የጠየቅኸኝን ሰዎች በአሁኑ ጊዜ አልክልህም ። ኢጣሊያኖችንም ለመዋጋት የምትችል አይመስለኝም ። ስለዚህ ውጊያውን ባትጀምር ጥሩ ይመስለኛል ። ባንተ ስህተትም አገሪቱ እንዳትቃጠል አስብበት ። ስለዚህ የሚሻለው ነገርና የምመክርህ መንገዱን ከፍተህ እንድትተውለት ነው ።

ደጃዝማች አበራ ካሣ

ራስ አበበም ይህ ደብዳቤ እንደደረሳቸው የደጃች አበራን ሁኔታ እንዲያጣሩላቸው ያኔ ኢጋፋሪ ይባሉ የነበሩትን ደጃች ያረጋልን ላኩዋቸው ። ደጃች ያረጋልም ከደጃች አበራ ዘንድ ሄደው ሲመለሱ “.........ተዋግተን ኢጣሊያን የምናሸንፍበት ጊዜ ገና ነው ። አሁን ከኢጣሊያኖች ጋር ውጊያ ስንገጥም መልሱ ቤታችንን ፣ ሰብላችንንና ከብቶቻችንን ማቃጠል ሆነ ። እኔ አሁን ወደ እንሳሮ ቆላ ስሄድ ኢጣሊያኖች በሰላም ደነባ ይገባሉ ። ስለዚህ መልካም የሆነላቸው ይመስላቸዋል ። ከዚህም በኋላ የሰላሙ ንግግር በራስ ኃይሉ አማካኝነት ይጀመራል ። ይህ እንግዲህ ለኔ የማደርገውን ውሳኔ ለመወሰን ጊዜ ስለሚሰጠኝ ባሁኑ ጊዜ ከኢጣሊያኖች ጋር

አልገጥምም ። ለወደፊቱ አብረን እንደምንሠራ ባውቅም ባሁኑ ጊዜ ግን ጦርነት አያስፈልግም .........” የሚል መልስ ይዘው መጡ ።

በጀኔራል ትራኪያ የሚመራው ጦር ያለ ምንም ተቃውሞ ታህሣስ 7 ቀን ደነባ ገባ ። ራስ ኃይሉም የማስታረቁን ጉዳይ ጀመሩ ። በደጃች አበራ ውስጥ ሰባ ያህል የሚሆኑ ሆለታ ጦር ትምህርት ቤት የተማሩ ወጣቶች ስለነበሩ የደጃች አበራን እቅ ጣጫ ሲያውቁ ከድተው ወደ ልጅ ኃይለማርያም ማሞ ዘንድ ገቡ ። ደጃች አበራም ለኢጣሊያኑ ጦር መሪ ደብዳቤ ጻፉ ።

ይድረስ ከደብረ ብርሃን ለሚመጣው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ፣

እኔ እጄን የምሰጥበትን ሁኔታ ከግራዚያኒ ጋር በመነጋገር ላይ ነኝ ። አሁን ባንተ መሪነት ወደኛ የሚመጣው ወታደርህ ቤት ማቃጠሉን ፣ ከብት መዝረፉንና ሰላማዊውን ሕዝብ ማስቸገሩን ሰማሁ ። ሰላማዊው ሕዝብም ራሱን ለማዳን መከ ላከል አድርጓል ። እንዲህ ዓይነቱ አድራጎት እንዲቆም እጠይቃለሁ ።” የሚል ደብዳቤ ላኩ ። የኢጣሊያኑ ጦር መሪ ጀኔራል ትራኪያም “ይድረስ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ፣ ከግራዚያኒ ጋር የሰላም ድርድር መጀመርዎን የገለጡበት ደብዳቤዎ ሲደ ርሰኝ በጣም ደስ አለኝ ። እውነተኛ ሰላማዊ ሰው መሆንዎን የማውቀው ግን ወታደሮችዎን ፍቼ ከተማ አሰልፈው በአደባባይ ሲቀበሉኝ ነው ። ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ቢሆኑ ሕይወትዎ እንደማይጠፉ በመንግሥቴ ስም ቃል እገባለሁ” የሚ ለውን ደብዳቤውን በልጅ ኃይለ ማርያም ገዝሙ እጅ ላከ ። ደጃች አበራም “ይድ ረስ ከጀኔራል ትራኪያ ፣ ለሕይወታችን ዋስትና ገብተው የላኩልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ ። ሰላማዊ ሰው በመሆናችን ቢዲጉን ከተባለ ቦታ በሰላም በሰልፍ የምንቀበልዎ መሆ ኑን ይወቁት” ሲሉ መልስ ላኩ ።

ይህ ከመሆኑ በፊት ደጃች አበራ ካሣ ለግራዚያኒ ለጻፉት ደብዳቤ ግራዚያኒ መልስ ጽፎላቸው ስለነበር ያን ደብዳቤ ነው ለጀኔራል ትራኪያ የሰላም ንግግር ጀምሬአለሁ ያሉት ። ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር ።

አዲስ አበባ ።

ዲሴምበር 11 ቀን 1936 ዓም 15ኛ ዓመተ ፋሺስት ።

ይድረስ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ።

ከሰላምታዬ በኋላ በራስ ኃይሉና በደጃዝማች አመዴ በኩል የላኩልኝ ደብ ዳቤ ደርሶኛል ። ከዚህ በፊት እንደሚያውቁኝ አውቃለሁ ። አሽከሮቼን ሊቢያ ውስጥ እንዴት አዝዝ እንደነበር በሚገባ ሳያውቁ አልቀሩም ። የዚህም አገር ሰው የሚ ናገረው ስለማይለወጠው ቃሌ ነው ። አሁን የምልዎት ምንም ነገር አይደርስቦት ምና እጅዎን በሰላም ይስጡ ። ለአገርዎ ተዋግተዋል ። በዚህም ማንም አይወቅስ ዎትም ። ለምን በከንቱ ታልቃላችሁ ? ወንድምዎ አስፋወሰንም ወደዚህ እንዲመጣ ልኬበታለሁ ። እንደሚያውቁት ላሊበላ ውስጥ እጁን ሰጥቷል ። ከጥቂት ቀናት በኋ ላም እዚህ ይገባል ። እንደደረሰም መድረሱን እጽፍሎታለሁ ። ከዚያም በኋላ እር ስዎም ሳይዘገዩ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ ። እስከዚያው ድረስም እዚያው ሆነው የሸዋ ሕዝብ በሰላም የሚኖርበትን መንገድ ያዘጋጁ ።

ሩዶልፍ ግራዚያኒ

ደጃች አበራ ካሣ እጃቸውን እንዳይሰጡ ብዙ አርበኞች መከሩዋቸው ። እሳ ቸው ግን የሁሉንም ምክር ትተው ታህሣስ 12 ቀን እጃቸውን ሰጡ ። በዚያው እጃ ቸውን በሰጡበት ቀንም ከወንድማቸው ከአስፋወሰን ካሣ ጋር ፍቼ ከተማ ውስጥ ተገድለው ራሳቸው ተቆርጦ ለሕዝብ ሲታይ ከረመ ።

ግራዚያኒም ታህሣስ 12 ቀን በቴሌግራም ቁጥር 8684/334444 "... በጦሬው ዕለት ወንድማማቾቹ አበራና አስፋወሰን ካሣ ተያዙ ። በኔ ትዕዛዝም ፍቼ ከተማ በአደባባይ ተገደሉ ። የሰላሌ ነገር ጉዳይ እንግዲህ አበቃ ። " በማለት አስተላለፈ ። አርበኝነቱ ግን ተጠናከረ ። የአርበኞቹም ኃይል ተጠናክሮ በኅዳር ወር 156 ኢጣሊያውያን ሲገድሉ በታህሣስ ወር ደግሞ 134 ገድለዋል ።

ታህሣስ 6 ቀን ራስ እምሩ በጄኔራል ማልታ በሚመራው ጦር ተያዙ ። ግራዚያኒም በቴሌግራም ቁጥር 32507 "......ራስ እምሩ እጁን ሰጥቶ በእግር ብረት ታስሯል ። ድል የሆነውም በፕሪንስቫል ወታደሮች ነው ። እኔም የጦር እስረኛ አድርጌዋለሁ ። በቅርብ ጊዜም ይገደላል" የሚል ቴሌግራም ወደ ሮም አሳለፈ ። ራስ እምሩም በአይሮፕላን ሆነው አዲስ አበባ አይሮፕላን ማረፊያ ከጧቱ በሶስት ሰዓት ሲደርሱ ብዙ ኢጣሊያኖች እየተከተሉ "ውሸታም ፣ ገዳይ" እያሉ ጮሁባቸው ። ባልታወቀ ምክንያትም ሞቱ ቀርቶላቸው እንዲታሰሩ ሆነ ።

አሁን ከታወቁት መሀል የቀሩት ራስ ደስታ ዳምጠው ፣ ደጃች በየነ መርዕድና ደጃዝማች ገብረማርያም ናቸው ። የእነኚህ ሦስት ሰዎች ሠራዊትም ከሰኔ 19 ቀን 1928 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 17 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ በሺ የሚቆጠር የኢጣሊያን ሠራዊት መፍጀታቸውን ራሳቸው ኢጣሊያኖች አምነዋል ።

ከጋዜጠኛው ፖጃሊ ማስታወሻ ላይ ብጠቅስ ፣ ፌብሩዮ 3 በያዘው ማስታወሻ "......ከራስ ደስታ ጋር ከገጠመው ጦር 200 ወታደርና ሰባት መኰንኖች እንደ ሞቱብን ተነገረን ። እንዲህ ዓይነቱንም የጦር ወሬ ለዓለም እንዳናሰራጭ ጋዜጠኞችን ሁሉ ሰብስበው ግዴታ አስፈረሙን ። ምክንያቱም ሮማ ላይ ከዚህ በፊት የወጣው መግለጫ "ጦርነቱ ተፈጽሟል" የሚል ስለነበረ ነው ። ....." ይልና ፌብሩዮ 7 በያዘው ማስታወሻ ደግሞ "........ቁርሴን አቃቂ ካለው ራዲዮ ጣቢያ እንደበላሁ ይርጋለም ያለው ጦራችን ከራስ ደስታ ጦር ጋር ገጥሞ እንደገና ሰባት መኰንኖችና 300 ወታደሮች እንደሞቱብን በራዲዮ ሲተላለፍ ሰማሁ ። .... " ይላል ። በዚህ አስቸጋሪነታቸውና አልበገር ባይነታቸው ምክንያት በገሌሶ ፣ በቱቼ ፣ በጋሊና ፣ በናታሊ ፣ በፖስኮሊኒ እና በራጋዞኒ የሚታዘዙ የጦር ብርጌዶች እንዲከታተሉዋቸው ተደርጓል ።

የካቲት 12 ቀን በካፒቴን ቱቼ የሚመራው የጠላት ጦር ጉጀቴ ላይ ከእነኚህ ጀግኖች ጋር ውጊያ ገጠመ ። በዚያም ውጊያ ደጃች ገብረማርያምና ሽመልስ ሀብቴ ተገደሉ ። በየነ መርዕድ ቆስለው ተማረኩና በኋላ ተገደሉ ። ራስ ደስታ ግን አመለጡ ። የኢጣሊያ ወታደር ራስ ደስታን እግር በእግር እየተከታተለ የካቲት 17 ቀን ኢያ ከተባለ ቦታ ተያዙ ። ራስ ደስታ የተያዙት በባንዳው መሪ በደጃች ተክሉ ጦር ነው ። ከዚያም ወደ ቡታጅራ ተወሰዱ ።

ራስ ደስታ ቡታጅራ እንደደረሱ ካፒቴን ቱቼ የሞት ፍርድ እንደተፈረደባቸው ነገራቸው ። ለራስ ደስታ የሞቱ ፍርድ ከተነገራቸው በኋላ የኢጣሊያኑ ደጃች ተክሉ መሸሻ ፣ ገዳይ ጓዶችን እንዲያዘጋጁ ካፒቴን ቱቼ አዘዞ የሞት ፍርዱ ከተነገራቸው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የካቲት 17 ቀን ተገደሉ ። ካፒቴን ቱቼም በቴሌግራም ቁጥር 750/24 «ዛሬ ፌብሩዮ 24 ቀን በ0600 ሰዓት ራስ ደስታ ዳምጠው ተይዞ ነበር ። ከቡርነትዎ እንዳዘዙት በ1730 ሰዓት በጥይት ተገድለዋል» የሚል ቃል ለግራዚያኒ አሳለፈ ። የኢጣሊያ አገር ጋዜጦችም ዜናውን በትላልቅ አርእስት እያደረጉ አወጡ ። የራስ ደስታም ሆነ የሌሎቹ መገደል የአርበኞችን ኃይል እያጠናከረው ሄደ ። በተለይ ከየካቲት 12 ቀን የአዲስ አበባው እልቂት በኋላ ተንገዳግዶ ሊወድቅ የነበረው ያአርበኞች ኃይል ተጠናክሮ ከማይበገርበት ደረጃ ደረሰ ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ የወጡትን የአርበኞች ኃይል ሊያጠናክር የቻለው የኢጣሊያኖች የግፍ ሥራ ነው ። በሰላም እርሶ የሚኖረውን ሰላማዊ ሕዝብ ሁሉ

በመጨረሳቸው ነግ በኔ በማለት ፣ ገብሮ የነበረው ሕዝብ ሁሉ እየከዳ ወደ አርበ ኝነት ገባ ። ከኢጣሊያ የግፍ ሥራዎች ጥቂቶቹን እንመልከት ።

የሐረርጌው ገዥ ጀኔራል ናዚ በውስጡ ላሉት የጦር መኰንኖችና የጦር መሪ ዎች ሁሉ የካቲት 23 ቀን ባስተላለፈው ቴሌግራም «....ክቡር ድል አድራጊው መሪ ፣ የዱቼን ትእዛዝና በሽፍቶች ላይ ስላላቸው ቁርጥ ውሳኔ ትእዛዝ ደርሶኛል። በዚያ መሠረትም እኔ አዛለሁ ፣ ሁሉንም ጨርሳችሁ ግደሉ ። እደግመዋለሁ ። ሁሉ ንም ። ሽፍቶች ፣ የተከበሩ ሰዎች ፣ ሹማምንትና ተከታዮቻቸውን ፣ በጦር ሜዳ የተ ማረኩትን ፣ ከምርኮ መንደራቸው ሸሽተው ወጥተው የተመለሱትን ፣ በየቤታ ቸው የተደበቁትን ፣ እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች የደበቁትን ፣ በማንኛውም መንገድ ለሽፍቶቹ ዕርዳታ የሚያደርጉትን ፣ የጦር መሣሪያ የደበቁትን ሁሉ ግደሉ ። የተ ለየ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ሴቶችም ሆኑ ልጆች ይገደሉ ።..... ዋናው አዛዥ ያስተላለፉት ትእዛዝ«ተገድለዋል» ብዬ መልስ እንድሰጥ ስለሆነ እናንተም በዚሁ ቃል መልስ ስጡኝ ።....» የሚል ትእዛዝ አስተላለፈ ።

ማርሻል ግራዚያኒ እንዲህ ዓይነቱን ትእዛዝ ያስተላለፈው ለጀኔራል ናዚ ብቻ ሳይሆን ለመላው ከፍተኛ የጦር አዛዦች በሙሉ ነበር ። መጋቢት 30 ቀን ለጂማው ገዥ ለጀኔራል ጂሴሶ የተላለፈለት ትእዛዝ «....የዱቼ አላማ ...ሁሉ እንዲጠፋ ነው ። .... ስለዚህ በአጠገብዎ ላሉ የወታደር አለቆችና ሲቪል ሠራተኞች ሁሉ ይህን የዱቼን አላማ እንዲያሳውቁ ይሁን ። ክብርነትዎን የማስጠንቀቀው ይህን ነገር በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲፈጽሙ ነው ። የሚያስፈልግዎ ነገር ካለ ማለ ትም ወታደርም ሆነ የጦር መሣሪያ የሚያስፈልግዎ ቢሆን ይጠይቁ ።.....» የሚል ነበር ።

ይህን የመሰለው ትእዛዝ በመላ ኢትዮጵያ ከተላለፈ በኋላ የሐረርጌው ጀኔራል ናዚ ለታዘዘው ትእዛዝ ሚያዝያ 15 ቀን ለግራዚያኒ በቴሌግራም መልስ ሲሰጥ «... በትእዛዙ መሠረት 600 ሹማምንትና ተከታዮቻቸው በባሌ ውስጥ ተገድለዋል። ...» አለ ። ከናዚ ሪፖርት በፊት ግራዚያኒ መጋቢት 22 ቀን ወደሮማ ባስተላለፈው ቴሌግራም«.....ከትእዛዙ ወዲህ 1439 ሰዎች ተገድለዋል ።....» ብሏል ።

ግራዚያኒ በቴሌግራም ቁጥር 5512 ሮም ላለው ለቅኝ ግዛት አገሮች ሚኒስ ትር ሲያሳውቅ«.....የጀኔራል ማሪዮቲ ጦር በግምት 500 የሚሆኑ የሣር ክዳን ቤቶ ችን አቃጥሏል ። ከ22 የሚበልጡ በኩብት በረት ውስጥ ተደብቀው የተገኙ ሰዎች በጥይት ተገድለዋል ። 300 የሚሆኑ ሰንጋዎችን ወታደሮቻችን ዘርፈዋል ። ከቀትር በፊት በአንድ ሰዓት የጦካንን ቀበሌ የማቃጠሉና የመዝረፉ ሥራ ቀጥሏል ።....» ብሏል ።

ጭካኔያቸውን ወደኋላ መለስ ብለን ብናይ ግራዚያኒ ለቅኝ ግዛት አገሮች ሚኒስ ትር በቁጥር 5554 ያስተላለፈው ቴሌግራም « በቁጥር 22914 ለጀኔራል ጋሊና ባስተላለፍኩት ቴሌግራም እንዳዘዝኩት የጀኔራል ማሪዮቲ ወታደሮች እንዳችም እንቅፋት ሳያገኛቸው ጥቅምት 18 ቀን ከቀትር በኋላ በ11 ሰዓት ባልጭ ገብተ ዋል ። አገሩንም ምንም ሰው የሌለበት ባዶ ሆኖ አግኝተውታል ። ቁጥራቸው በጣም ያነሱ ሰዎችን ብቻ አግኝተው ስለነበር እነሱን እዚያው በጥይት ደብድበ ዋቸዋል ። ጠላትም ወደ ሰሜን ያመራ ይመስለኛል ። ዛሬ ጥቅምት 29 ቀን ወታ ደራችን ረፍት አድርጎ አገሩን በመበርበርና በማቃጠል ይውላል ።» ሲል አሳው ቋል ።

በተለይ የካቲት 12 ቀን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በግራዚያኒ ላይ አደጋ ከተ ጣለበት በኋላ ግራዚያኒ እንደ እብድ ሆነ ። ለሊት በመባነን እየጮኸ ስለሚያድር ቤተ መንግሥቱ በከባድ ሽቦ አጥር ታጠረ ። በታንኮች በተጠናከረ ፣ መትረየስ በያዙ

ዘቦች በአንድ ባታሊዮን ጦር እንዲጠበቅም ተደረገ ። ይህም ሆኖ የግራዚያኒ ፍርሐት እያየለ በመሄዱ ኢትዮጵያውያኖችን በማስጨረስ ተግባሩ ላይ በረታ ።

ኢጣሊያ ኢትዮጵያ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ በ11 ወር ጊዜ ውስጥ ማለት ከግንቦት ወር 1928 ዓ ም ጀምሮ እስከ መጋቢት ወር 1929 ዓ ም ድረስ 950.700 ኪሎ ግራም የሚመዝን ፈንጂ ከአይሮፕላን ብቻ ጥላለች ። ይህ በአስራ አንድ ወር ውስጥ የተጣለው ቦምብና የመርዝ ጋዝ በመሬት ለሚተኮሰው ጥይት ረዳትነት ነው ። ይህ ሁሉ ሆኖ የአርበኞቹ ኃይል እያየለ እንጂ እየደከመ አልሄደም ።

ሊ አናሊ ዴል አፍሪካ ኢታሊያና የተባለው የኢጣሊያ ጦር ወሬና ሌላም የሚተነትነው እስታስቲካዊ መጽሐፍ «.....የክረምቱ መግቢያ ሲደርስ እንደተለመደው የሽፍቶቹ ኃይል በረታ ። በተለይ በላስታ በደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ፣ በደቡብ ጉጂም በደጃዝማች መንገሻ ፣ በምሥራቅ ጉጂም በበላይ ዘለቀ የሚመራው ጦር ከብዶብን ነበር ። .....ብዙም ጉዳት አደረሰ ።.....» በማለት ገልጾታል ።

—— O ——

DATI RIASSUNTIVI SULL'ATTIVITÀ BELLICA SVOLTA DAI REPARTI DELL'AERONAUTICA A. O. I.

DURANTE IL PERIODO MAGGIO 1936 XIV. - MARZO 1937 XV.

| DATA | | BOMBARDAMENTI E RICOGNIZIONI OFFENSIVE | | | ESPLORAZIONI E COLLEGAMENTI | | TRASPORTI PER RIFORNIMENTI AI PRESIDI ED ALLE COLONNE OPERANTI | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ANNO | MESE | Numero di voli | Ore di volo | Esplosivo lanciato tonnellate | Numero di voli | Ore di volo | Numero di voli | Ore di volo | Munizioni - viveri - materiali vari - tonnellate | Persone trasportate numero |
| 1936 | Maggio | 363 | 708,30 | 53,6 | 122 | 340,50 | 805 | 2252,05 | 361,3 | 1781 |
| » | Giugno | 293 | 828,00 | 32,1 | 227 | 659,55 | 608 | 1681,20 | 253,2 | 1507 |
| » | Luglio | 384 | 1082,30 | 55,2 | 168 | 538,50 | 558 | 1812,45 | 234,0 | 1121 |
| » | Agosto | 375 | 1043,05 | 82,5 | 375 | 1206,35 | 702 | 2055,15 | 334,3 | 1134 |
| » | Settembre | 272 | 887,15 | 56,5 | 191 | 562,20 | 431 | 1160,15 | 202,4 | 860 |
| » | Ottobre | 197 | 392,15 | 194,1 | 321 | 612,00 | 134 | 564,25 | 136,9 | 410 |
| » | Novembre | 218 | 586,35 | 181,4 | 462 | 974,10 | 99 | 502,00 | 120,6 | 377 |
| » | Dicembre | 185 | 462,55 | 49,5 | 998 | 2548,35 | 425 | 1148,00 | 180,3 | 840 |
| 1937 | Gennaio | 587 | 1243,20 | 126,0 | 611 | 1703,40 | 323 | 901,05 | 1351,0 | 1354 |
| » | Febbraio | 402 | 1033,00 | 90,3 | 367 | 771,10 | 282 | 804,45 | 91,0 | 1028 |
| » | Marzo | 377 | 838,10 | 29,5 | 619 | 1397,55 | 281 | 736,55 | 144,0 | 1485 |
| | TOTALI | 3653 | 9105,35 | 950,7 | 4463 | 11316,00 | 4648 | 12618,50 | 2193,1 | 11897 |

RIEPILOGO GENERALE

Numero voli: 12764. Persone trasportate: 11897.

Materiali trasportati o lanciati tonnellate: 2193,1. Esplosivo lanciato tonnellate: 950,7.

Ore di volo: 33040,25.

ባንድ ዓመት ከአይሮፕላን የተጣለ ቦምብ የሚገልጽ እስታቲስቲክስ ።